

ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደላቸው ።

# ትንሣኤ



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችና መላእክት እያዩት በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ።

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 21 ፲፱፻፸፩

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ሬሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ስም ያለ ግብር | ፪ |
| ዳንኩኝ የምሥራች | ፫ |
| ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር | ፬ |
| በጉብዝናህ ወራት | ፯ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፰ |
| የሃይማኖት ዓምድ | ፱ |
| ቤተክርስቲያንና ቅርሶችዋ | ፲ |
| እውነተኛ ፍቅር | ፲፪ |
| የጤና ዓምድ | ፲፫ |
| የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች | ፲፬ |
| ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ | ፲፭ |
| የሴቶች ዓምድ | ፲፯ |
| ክርስቲያኖች ከጋብቻ በፊትና በኋላ ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ | ፳ |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና | ፳፩ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፳፪ |
| የተፈጥሮ መረዳዳት | ፳፫ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል ? | ፳፬ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

መላእክትን ለምን እናከብራቸው አለን? በእነርሱ ስምስ ምጽዋትና ዝክርን ለምን እናደርጋለን?

ወይዘሪት ቆንጂት ወርቁ
ከአዋሳ ቅ/ገብርኤል የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር
አዋሳ

● ወይዘሪት ቆንጂት ስለ ጥያቄሽ እናመሰግንሻለን ። በጥያቄሽ መሠረት መላእክትን የምናከብርበት ምክንያት ሰዎችን ለመርዳት የሚላኩና የሚያገለግሉ ስለሆኑ ነው ። ዕብራውያን 1፡14 ። መላእክት ዘወትር በሰማያት ባለው በእግዚአብሔር ፊት ስለ ድሆች ይቆማሉና በስማቸው ለድሆች ምጽዋት እንሰጣለን ። ስለዚህም የሚከተለውን ጥቅስ እንድታነቢ እጋብዝሻለሁ ማቴ.18፡10 ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ የወንድምነት መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን ዐሥራት ማውጣት እንደሚገባ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ አለ ። ነገር ግን በእኛ ቤ/ክርስቲያን ይህ ነገር እስከዛሬ በሚገባ አልተለመደም ። አማንያንም ዐሥራት ከማውጣት ይልቅ ድግስ ደግሶ ማብላትን ብቻ ይመርጣሉ ። አብዛኛዎቹ ሃይማኖታቸውን ለማክበር ሳይሆን በሞቱ ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደርስላቸው ልጅ በወለዱ ጊዜም ክርስትና እንዲያስነሡ አራት ብር ብቻ ይሰጣሉ ። እኔ በዓይኔ እንዳየሁ ማንኛውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ዐሥራት ማውጣት ይቅርና ሕይወትን እስከመስጠት ድረስ ድርጅቱን እንደሚረዳ ተረድቻለሁ ። ታዲያ እኛስ"ርትዕት ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ" የአባቶቻችን ሃይማኖት የቀናች ናት እንደተባለ ሁሉ ለቀናች ሃይማኖታችን ዐሥራት ቀርቶ ሌላ መሥዋዕትነት ከፍለን ቤተ ክርስቲያናችንን ራስዋን ማስቻል አይገባንምን?

ደምሴ በቀለ ከአዋሳ

● አቶ ደምሴ በቀለ ጥልቅ መንፈሳዊ ቅንዓት ስለተሞላው ጥያቄዎ እጅግ እናመሰግንዎአለን ዐሥራት ማውጣት ለክርስቲያኖች ተገቢ ነው ። በማንኛውም የክርስቲያን ዓለም የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደረው ከተከታዮችዋ በሚገኝ ዐሥራት እንጂ ሌላ ገቢ የላትም ቤተ ክርስቲያናችንም በአሁኑ ጊዜ ሰበካ ጉባኤ የምታቋቁመው ይህን ዓይነት ሥርዐት ለምእመናኖችዋ ለማለማመድ ነው ። ስለዚህ ምእመናን ሁሉ በሞት ጊዜ አራት ብር ከመስጠት ይልቅ በሕይወት ሳሉ ከሚያገኙት ገቢ ዐሥራት መክፈል ባይችሉም በመጠኑ ለቤተ ክርስቲያናቸው አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ እኛም እንደ እርስዎ እናሳስባለን ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ሰላም በጌታችንና በመድኃኒታችን ለእኛ ሲል በቀራንዮ በተሰቀለው በጌታችን ኢየሱስ ለእናንተ ለመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቼና እኅቶቼ ይሁን ።

ከሰላምታዬ ቀጥዬ የምለምናችሁ ነገር እንደሚከተለው ነው ። በወለጋ ክፍለ ሀገር በነቀምቴ ከተማ በነበረው የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር አባል ነበርኩ በብዙ ፈተናና ትግል ስከታተል ነበርሁ ነገር ግን ግንቦት 28 ቀን 1970 ዓ.ም.እናቴና ወንድሜ ሞቱብኝ። ከዚያጊዜ ጀምሮ ከዘመድ ርቄ ከቤተ ክርስቲያንና ከክርስቲያን እኅቶችና ወንድሞች ተለይቼ አጽናኝ አጥቼ እኖራለሁ ። በአካባቢዬ ባለው መንፈሳዊ ማኅበር ለመካፈል ነፃነት ስላጣሁ ከጌታ መንገድ እንዳልርቅ በተቻላችሁ መጠን ርዳታችሁን በአንዳንድ የጽሑፍ መልእክት ትረዱኝ ዘንድ በጌታ ስም አደራ እላለሁ። የምኖረው ከወንድሜ ጋር ነው ፤ ፈቃድ ስጠይቀው ብዙ ምክንያት በመፍጠር ሊፈቅድልኝ አልቻለምና አደራዬ የጠበቀ ነው የጌታን ቃል ተጠምቻለሁና ። በመንፈስ ቅዱስ እኅታችሁ

ተማሪ ተናኘ ገ/ሥላሴ
ክ.ተ.ወ.መ.ማ
የመ.ሣ.ቁ.33 ባሕር ዳር ጐጃም

● ተማሪ ተናኘ ገ/ሥላሴ እናትሽና ወንድምሽ ስለሞቱብሽ ተስፋ የሚያስቆርጥ ኀዘን ማዘን አይገባሽም ። እናት ወይም አባት ወንድም ወይም እኅት ያልሞተበት ግለሰብ በዓለም ላይ አይገኝም ይልቁንም ሁሉም በአንድ ጊዜ የሞቱበት ሰው ይገኛል ።

ወደቤተ ክርስቲያን እንዳትሄጂና ቃለ እግዚአብሔርን እንዳትሰሚ በመንፈሳውያን ማኅበራት ተሣታፊት እንዳትሆኚ ፈቃድ ማጣትሽ እጅግ ያሳዝናል ፣ እኛንም አሳዝኖናል ። ስለዚህ በዚህ አጋጣሚ ወንድምሽ ፈቃድ እንዲሰጡሽ አደራ እንላለን ። ምናልባት አንችን ለመቆጣጠር ከፈለጉ አብረውሽ ቢሄዱ ለርሳቸውም ለአንችም መልካም ዕድል ይሆናል ። እርሳቸው ከአንቺ ጋር ለመሄድ ፈቃደኛ ካልሆኑ ደግሞ እንደ አንቺ ያሉ ሌሎች በዚያ አካባቢ ስለማይጠፉ ከእነርሱ ጋር ትሄጂ ዘንድ እንዲፈቅዱልሽ በድጋሚ በጌታ ስም እንጠይቃቸዋለን ፤ ከዚህ ሌላ ተናኘ በጽሑፍ እርዱኝ ስላልሽ ምን ዓይነት ጽሑፍ እንደምትፈልጊ ብትገልጭልን ለመላክ ፈቃደኞች መሆናችንን በደስታ እንገልጥልሻለን ። ጌታ ከአንቺ ጋር ይሁን ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

1ኛ/ የኢትዮጵያ ባህል በሃይማኖት በኩል በዐመት አንድ ጊዜ የጥምቀት በዓል ሲከበር በብዙ የሚቆጠሩ ጽላቶች ከመቅደሳቸው ወጥተው በየተወሰኑላቸው ቦ

ወደ ገጽ ፭ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእስ አንቀጽ

### ስም ያለ ግብር

ስም ግብርን ይከተላል ። በተለመደው አነጋገራችንም ስም ወደ ግብር ይመራል ይባላል ። ነገሩን ግልጥ ለማድረግ እንዲህ እንበል አንድ ሰው መምህር ይባላል ያስተምራልና ፣ ሌላው ደግሞ ገበሬ ይባላል ። ያርሳልና ፣ ከብትንም ያረባልና ። ግን የማያስተምረው ሰው መምህር ቢባል ቅጽል ስሙ ሥራውን እንደማያ መለክት መረዳት አያስቸግርም ። እርግጥ የማስተማር ችሎታ እያለው በግብርና ሥራ ቢሠማራ ገበሬ ይባ ላል እንጂ መምህር ተብሎ ሊጠራ አይችልም ። በዚህ አንጻር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ስለሚገኘው ግብር የለሽ ስም ለመግለፅ እንፈልጋለን ።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቄስ ወይም መምህሬ እንደዚ ሁም አባ የሚባሉ አያሌ ግለሰቦች አሉ ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች የሚያገለግሉበትና ወንጌል የሚያስተም ሩበት ቤተ ክርስቲያን የላቸውም ። ምእመናንም እንደ መንፈሳዊ አባት የሚመለከቱአቸው አይመስልም ። ምክንያቱም በተወሰነ ቤተ ክርስቲያን አያገኙአቸውምና ። ከዚህም ጋር ለስም ብቻ ቅስና የተሰጣቸው ካህና ት በእሁድም ሆነ በሌላ የቤተ ክርስቲያን በዓል ቀን በቤታቸው ያረፍዳሉ ። ለምን? በዚያ ቀን እንዲቀድሱ እንዲሰብኩና ሌላም ቤተክርስቲያናዊ አገልግሎት እንዲያደርጉ ኃላፊነት አልተሰጣቸውምና እርግጥ በተጋባ ዥነት መልክ በየትም ቦታ ሄደው ማስተማር ይችሉ ይሆናል ። ይህም የጥንቱን የቶፋነት ሥርዓት ያንፀባር ቃል እንጂ እውነተኛ ክህነታዊ ሥርዓት መስሎ አይታይም ። በመሠረቱ መሆን ያለበት አንድ ዲያቆን ለቅ ስና መዓርግ የሚበቃ መሆኑ በምእመናን ሲረጋገጥ በቅድሚያ የሚያገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ይፈለጋል ፤ ቤተ ክርስቲያኑ ሲገኝ የክፍሉ ጳጳስ ወደዚያ ቦታ ይሄዳል ፣ የሰበካው ምእመናንም በቅስናው የበዓል ሥነ ሥር ዓት ላይ ይገኛሉ ፤ ጳጳሱም ከዚያ ቀን ጀምሮ ቄሱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠባቂያቸውና አገልጋያቸው መሆኑን ይገልጥላቸዋል ። እነርሱም ፈቅደው ይቀበሉታል ፤ ከዚህ በኋላ ቄሱ የሚያገለግልበትን ቤተ ክርስቲ ያን የሚያገለግላቸውንም ምእመናን አገኘ ማለት ነው ። በዚህ ጊዜ ስም ከግብር ግብርም ከስም ይስማማል ። እንደዚህ ካልሆነ ግን ቀሲስ እገሌ ወይም አባ እገሌ የሚለው ስያሜ እንደቀልድ ስም የሚቆጠር ይመስለናል የቤተ ክርስቲያንንም መዐርግ ያዋርዳል ይህ ብቻ አይደለም ቄሱ በቅስና ሙያው ዘወትር የማገልገል ኃላ ፊነት ስለሌለው አንድ ጊዜ በኮትና በክራባት ፣ በሌላ ጊዜ በቀሚስ ፤ በካባ በጥምጥምና በቆብ ይታያል ። ቄስ ተብሎ እንዳይጠራም የሚናገርበት ጊዜ አለ ። ይህ ሁሉ ችግር ለምን ተፈጠረ ? እዎ ቤተ ክርስቲያን መዓርገ ክህነት ስጥታ የሥራ ቦታ በአለመስጠትዋ እንደሆነ እንገምታለን ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን ቅስና ከመስ ጠትዋ በፊት መንጋዎችንና መሠማሪያውን ቦታ ታዘጋጅ ፤ ቀጥላም እረኛውን ትመድብ ፣ ቅስና ከተቀበሉ በኋላ የሚያገለግሉበት ቦታ ካለመኖሩ የተነሣ ቀሲስና አባ እየተባሉ በሌላ ቦታ የሚያገለግሉ ጥቂቶች አይደሉ ም ። ምናልባት ቤተክርስቲያን እነዚህን ሰዎች እንደገና መልሳ ልትጠቀምባቸው አትችል ይሆናል ፤ እንግ ዲያውስ ካለፈው ድርጊት ትምህርት እየወሰደች ስለሚመጣው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋታል እንላለን ። "ነገ አቡኑ በዚህ በኩል ያልፋሉና ለዲቁናና ለቅስና ልጆቻችሁን እንድታወጡ" ይባል የነበረውን ለፈፋ ዛሬ ደግማ ማስተጋባት የለባትም ። ቅስና በዓዋጅ አይደለም ቅስና ለሮጠ ሳይሆን ለተጠራ ነው ቅስና ለራስ መገልገያ ሳይሆን ሌሎችንና ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ነው ። እንግዲያውስ የቅስና መዓርግ ተሰጥቶአቸ ው ቀስና አባ እየተባሉ የሚጠሩ ሁሉ ሌሎችን የሚያገለግሉበት ቦታ ይኑራቸው ስማቸውም በሥራ ይተር ጐም ፤ ስም ያለ ግብር ካህን ያለ ደብር አይሆንምና ።



## ዳንኩኝ የምሥራች

በ1964 ዓ.ም. ከአምቦ ተነስቼ በእግር ስጓዝ ሚጤ ከተባለው ቦታ ስደርስ በፈረን ጆች አባባል ነርብ የተባለ በሽታ ለከፈኝ በዚህ በሚጤ ከተማ የማውቀው ሰው ባለመ ኖሩ በአንድ እና ቤት ወድቄ ስሰቃይ በዚህ ከተማ ተቀማጭ የሆኑ አቶ ሙሉጌታ አበበ የተባሉና ሌሎችም በጐ አድራጊዎች የሆኑ ሕዝበ ክርስቲያን መንፈሳዊ ርዳታ አድር ገውልኝበመኪናከሚጤወደሀገረሕይወት ሆስፒታልአደረሱኝ፣በዚሁ ዓመተ ምሕ ረት የሆስፒታሉ አስተዳዳሪ የሆኑ ዶክተር ኰምላንድ የተባሉት በነፃ እንድተኛ አደ ረጉ ።

በዚሁ ሆስፒታል ዘጠኝ ወር ተኝቼ እካ



ለብዙ ዓመታት ሽባ ሆነው ከኖሩ በኋላ በዐበል የዳኑት አባ ፍቃደ ወ ማርያም ከነብርኩማቸው

ለ ስንኩል ወይም ሽባ ሆኜ ለጊዜው ሕመሜ ተቀንሶልኝ በታኅሣሥ 21 ቀን 65 ዓ.ም. ከሆስፒታል ወጣሁ ። የዚህም ሆስፒታል ሠራተኞች ሙሉ መንፈሳዊ ርዳታ አድ ርገውልኝ በራሳቸው መኪና በአቶ አስናቀ ንጉሤ ሾፌርነት ከሀገረ ሕይወት ወደ ወሊሶ መምህር ወልደ ትንሣኤ ግዛው ዘንድ አደ ረሱኝ መቸውንም የታመመ ሰው እድናለሁ እንጂ እሞታለሁ ስለማይል በጸበሉ ስነ ክር ለእመቤታችን ለእመብርሃን ክብር ምስጋና ይድረሳትና ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ፀጉሬ በሕጢአት ለተሸፈንኩት በጥር 20ቀን በተኛሁበት ቤት በራእይ አንዲት ቀይ ሴትዮ መልኳ እንደ ፀሐይ የሚያበራ የያዘችው ወንድ ሕፃን ልጅ መልኩ እንደ እሷ ሆኖ ሁለት ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበል ባልየሆኑ በቀኝ ጐኗ ይዛ "አንተ ሰው በመ ጀመሪያ ንስሐ ግባ ሂደህ ለመምሬ አበበ ንገር ከዚያ በኋላ እዚህ ሳይሆን አምቦ ሀገረ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ሂደህ ለምነኝ" ብላኝ ተሰወረች ።

እኔም ስነቃ ራእይ መሆኑን ስለተረዳሁ ይህንኑ ሕልም ለመምህር ወልደ ትንሣኤ ግዛው ገለጥኩላቸው ፤ እሳቸውም በሐዋር ያው ያዕቆብ መልእክት ምዕ.5 ቁ. 15 ላይ "የእምነት ጸሎት ድውዮችን ያድናል ጌታ ም ያነሣዋል ይላል" ስለዚህ በሕልም እንዳየ ኸው ወደዚያው አገር ሂድና ደጅ ጥና አሉኝ እኔም ምክራቸውን ተቀብዬ የድንግል ማር ያምን አማላጅነት ተማምኜ የኢየሱስ ክር ስቶስን መሐሪነት አውቄ ይህንኑ ሕልም ተስፋ በማድረግ በግንቦት 15 ቀን 1967 ዓ.ም. ከወሊሶ ወደ ሆለታ ገነት ኪዳነ ምሕ ረት መጥቼ ዐረፍኩ ፤ በዚሁም ቦታ በጦር ት/ቤትየሚገኙ የጦር ሠራዊት ለልብስም ሆነ ለምግብ እየረዱኝ እስከ ጥር 4 ቀን 68 ዓ.ም. ቆየሁ ፤ ጥር 5 ቀን 68 ዓ.ም. አምቦ ለመሔድ በተነሣሁ ጊዜ አቶ ገዝሙ ዘውዴ የተባሉት በጎ አድራጊ ለመኪና መሣፈሪያ ከፍለው ሸኙኝ ፤ እኔም በዚሁ መሠረት ሀገ ረ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት መጥቼ በዚሁ ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚገኙ ወ/ሮ ወር ቁ አበራ ለነፍሴ ይሆነኛል በማለት እስጠ ግተውኝ ጠበል እየተጠመቅሁና ጸሎት እያደረግሁ እመቤታችንን ስግጸን ለዓለም እናት ለሆነችው ድንግል ማርያም ክብር ምስጋና ይግባትና በግንቦት ወር ቀኑ እሁድ ለዘጠኝ አጥቢያ በሕልሜ ቀደም ሲል እዚያ ወሊሶ የታየችኝ እመቤታችን "ያመነ ይድ ናል ፤ በእኔም አማላጅነት ለሚተማመኑ



www.ethiopianorthodox.org


ሁሉ በችግራቸው ጊዜ እደርሳለሁ ፤ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስም ልመናዬን ተቀብሎ ለሁሉ እንደፍላጐታቸው ይሰጣቸዋል ። ስለዚህ ተነሥ ድነሀል ይህም ድኅነት የተሰጠህ ከእግዚአብሔር ነው አሁንም ሰውን አክብር እግዚአብሔርን ፍራ የእኔን አማላጅነት የኢየሱስ ክርስቶስን መሐሪነት በየደረስክበት ምስክርነትህን ንገር ብላኝ ተሰወረችብኝ እኔም ከእንቅልፍ ስነቃ ራእይ መሆኑን ተረዳሁ 4 ዓመት ሙሉ የታሰሩት እካሎቼ እንደማሽላ እየተንጣጡ - ተፍታቱ በላይ የጠቀስኳቸው የቤቱን ባለቤት ጠርቼ አንሱና ወደ ቤተ ክርስቲያን ውሰዱኝ አልኳቸው ፤ ወሰዱኝም በክርስቶስ መሐሪነት በኪዳነ ምሕረት አማላጅነት ከዚያ ሁሉ ደዌ ተላቅቄ 4 ዓመት ሙሉ በመቀመጫዬ የምታዩትን ጉማ አስሬ የምታዩትን ብርኩማ በቀኝና በግራ እጄ ይዤ መሬት ለመሬት እየተንፏቀቅሁ ሕዝበ ክርስቲያኑን እያስቸገርኩ የምኖረው ሰው አሁን ግን ምሕረት አግኝቼ 11 አካላቶቼ ሲፈቱ 12ኛ ምላሴ ለምስክርነት የእግዚአብሔርን መሐሪነት ለመመስከር ጨርሶ ሳይፈታልኝ አሁንምኩልታፋ ሆኜ እገኛለሁ። ስለሆነ ጨርሶ እግዚአብሔር እንደሚፈታኝ አምናለሁ ።

ስለዚህ ምስክርነቴን የምሰጠው ድንግል ማርያም በአማላጅነትዋ ለሚተማመኑ ሁሉ ፈጥና እንደምትደርስላቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ እንደምታማልዳቸው ለማረጋገጥ ነው ።

ይህም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ9 ከቁጥር 1 - 40 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዕውሩ ያደረገውን ምሕረት የተከተለ ነው ይህም ማለት "ሒድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ" ካለው በኋላ በሽተኛው ታጥቦ ከበሽታው ድኖ እያየ እንደተመለሰ ሁሉ እኔም በኪዳነ ምሕረት ጠበል ተጠምቄ ከበሽታዬ ድኛለሁ ።

ፈቃደ ወልደ ማርያም

ቅዱሳት መጻሕፍትን
በማንበብ
ነፍስዎንና
አእምሮዎን
ይመግቡ



የመጽሐፍ ቅዱስ
ማኅበር አባል
በመሆን
ማኅበሩን
ይርዱ ።

«... የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና ፤ የሚሠራም ፤ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው ፤ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል ፤ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል ፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ ፤ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» ።

ዕብራውያን ፬ ፡ ፲፪ ፲፫ ።

# ወርቃማዋ ቃል

**ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ ፤ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው ።**

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ።
☎ 122033 ⊠ 30750
አዲስ አበባ



## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ታ ላይ ያድራሉ ይኽን ሁሉ ከማድረግ ይልቅ የሚፈለገው ቃሉ ስለሆነ ከአመንበት ወንጌሉና መስቀሉ ለጥምቀት በዓል አይበቃም ወይ?

2ኛ በአሁኑ ጊዜ በሃይማኖትና በሳይንስ ስንከራከር ከመጨረሻው ፖይንት ላይ ሳንደርስ ክርክርህን "እባክህ ተወው ሳይንቲስቶች አንድ ኃይል አለ ብለዋል" በማለት እናቆማለን ይኽን ያለው ፈላስፋ የየት አገር ሰው ነው ስሙስ ማነው?

3ኛ/ ባህልና ሃይማኖት አንድ ናቸው ወይ አንድ ካልሆኑስ የሃይማኖት ባህሎች መሻሻል የለባቸውም?

ከደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተክርስቲያን
ዲያቆን ደስታ ሙሉጌታ

1/ በመጀመሪያው ተራ ቁጥር በበዓለ ጥምቀት ስለጽላቶች በጥምቀተ ባሕር ስለማደር በመጥቀስ ወንጌልና መስቀል ብቻ ቢበቃስ ለተባለው ጥያቄ ይህ መሆን የሚችለው ከአብዛኛው ካህናትና ምእመናን ድምፅ ተሰጥቶበት በቅዱስ ሲኖዶስ ሲወሰን ብቻ ነው ።

2/ ስለአንድ ኃይል መኖር ከተናገሩት የጥንት ግሪክ ፈላስፎች መካከል አናክሳጎራስ ነው ። እርሱም በ428 ከክርስቶስ በፊት ነበር ሶቅራጥስም በድጋሚ ተናግሮአል ። ብዙ ሳይንቲስቶችም ይህን ይደግፋሉ ።

3/ በመሠረቱ ባህል ሃይማኖት አይደለም ። በሁለቱም መካከል ልዩነት አለ ነገር ግን እያንዳንዱ አማኝ አምልኮቱን የሚገልጥበት የተለያየ ሥርዓት ወይም ባህል አለው ። ለምሳሌ በ1ኛው ተራ ቁጥር ጠያቂው ዲ/ደስታ እንደገለጥኸው እንኳ ለጥምቀትም ሆነ ለሌላ ዓመት በዓል በታቦት መውጣት አስፈላጊነት የሚያምኑ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ የሚፈለገው ቃሉ ስለሆነ ወንጌልና መስቀል ይበቃል የሚሉ የራሳቸው ባህል ያላቸው መሆኑን ያሳያል ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል ብሉይን በኋላም ሐዲስን ተቀብላ ትክክለኛውን እምነት ይዛ የምትኖር ናት በዚሁም አንጻር የዘመናትን ቁጥር በሱባኤ ነቢያት በቀመረ ሊቃውንት መነሻና መድረሻ ያለው አቆጣጠር አላት ይኸውም እስከ ልደተ ክርስቶስ እስከ ምጽአቱ እያለች 8 ሺህ ዓመታት ትቆጥራለች ።

ነገር ግን አንዳንድ ሃይማኖት ተከታዮች ምጽአተ ክርስቶስ ዛሬ ነው ነገ ነው እያሉ በየቦታው በእንባ ሲራጩ ይታያሉ ።

አሁን ደግሞ መምህር ኪዳነ ማርያም ገ/ሕይወት ከ1971 ዓ ም ጀምሮ ወደፊት ሁለት ሺህ 6 መቶ 42 ዓመታት እንዳሉ በአሳተሙት መርሐ አዝማን በተባለው የቁጥር መጽሐፍ በገጽ 138 ላይ ተገልጿል ። ለመሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን አቆጣጠር ነው ወይስ በሳይንቲስቶች አቆጣጠር ነው ስለዚህ እሳቸውም ሆኑ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የጉባኤ ሊቃውንትና በየ ክፍለ ሀገሩ የቁጥር ሊቃውንቶች ትክክለኛዉን አቆጣጠር ለመላዋ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲያስታውቁ ይጠይቁልኝ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ስም እጠይቃለሁ ።

አባ ተክለ ድንግል ደሴ

### ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

ለዚህ ጥያቄ ማንኛውም አንባቢ መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጥበት በመጽሔታችን አውጥተነዋል ። ስለዚህ መልስ ወይም አስተያየት ለመስጠት የሚፈልጉ ሁሉ በመልእክት ሣ.ቁ. 3137 አዲስ አበባ ቢልኩልን ይደርሰናል ።




www.ethiopianorthodox.org

# በጉብዝናህ ወራት

በማኅፀን ታንጾ ከእናቱ ከወጣ በኋላ የተወሰነለትን ያህል ሰንብቶ በመጨረሻው ቀን ሰው ወደ ምድር ማሕፀን ይመለሳል ራቁቱን መጥቶ ራቁቱን ይሄዳል ፤ የሰው ትርፉ ምንድነው ከየትና ለምን መጣ ወዴትስ ይሄዳል? ሌሎች ሌላ ቢሉ እኛ ግን ከእግዚአብሔር መጥተን ለእግዚአብሔር ክብር ኖረን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንድንሄድ እናውቃለን ይህንን ለማወቅ አእምሮ የሰጠን እግዚአብሔር ለዘመኑ ጥንት ለሕላዌው ፍጻሜ የሌለው ነው ለአምላካችን ፀንቶ ለሚኖረው ክብርና ምስጋና ይሁንለት ።

የእግዚአብሔር ፍቅር የዕድሜ ክልል የለውም ግን ብዙዎች በዘመናችን እግዚአብሔርን ለመከተል ቤተክርስቲያን ስትጠራቸው "ስሸመግል እደርስበታለሁ" የሚለውን ማስተዋል





ወጣቶች በጉብዝናቸው ወራት የእግዚአብሔርን ቃል ሲማሩና ለእግዚአብሔር ሲዘምሩ

የጐደለበት መልስ ሲሰነዝሩ ሕይወታቸውን በእጃቸው ያደረግዋት ይመስል ከአበው ከሐዋርያት ተግሣፅ ፈቀቅ ብለው ይታያሉ ። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ቅዱሱንም ዕውቀት ማስተዋል ነው ጠቢቡ ሲራክ ከሕፃንነትህ ጀምረህ ያልተመከርህ በእርጅናህ ጊዜ እንዴት ትሆናለህ? (25 ቁ.3) ሲል ሕያው ምክር ትቶልናል ። እግዚአብሔርን መከተል ገና ከሕፃንነት ወቅታት መሆኑን መዘንጋት ፈጣሪን ችላ ማለት ከመሆኑም በላይ አምላክን አለማወቅ ነው አበባ አበባነቱ ደስ የሚለውና የሚያስጐመጀው ገና በለግላጋንትና በአበባነት ጊዜ እንጂ ጠውልጎ ወደ መድረቅ በደረሰበት ሰዓት አይደለም ሰውም የወጣትነት ጊዜውን ከዓለም ጋር በመዋጋት ካሳለፈ በኋላ ሕሊናው ሞቶ ስሜትና ሥጋዊ ፍትወቱም በርዶለት ጤዛንቱ በኖ ጉልበቶቹ ዝለው ጀርባው ጐብጦ ቢሰርቅ ሮጦ ለማምለጥ እንኳ በማይችልበት ሰዓት ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ማለት ደጀ ሠላምን ማጣበብ ሆኖ እንዴት ተግሣፅን ጠላሁ ልቢም ዘለፋን ናቀ ያስተምሩኝ የነበሩትንም አልሰማሁም ጆሮዬንም ወደ መምህራኔ አልመለስሁም ያሰኛል ምሳሌ 5 ፡ 12 ።

ዘመን የማይሽረው የእግዚአብሔር መጽሐፍ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ ይለናል ኤርምያስ በእግዚአብሔር ለነቢይነት ሲጠራ "ወዮ ጌታ ሆይ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አልችልም" ኤር 1፡4-10 ሲል ታናሽነቱን በመግለጥ ከነቢይነት ለመሸሽ ተናገረ እግዚአብሔር ግን እኔ ካንተ ጋር ነኝና ብላቴና ነኝ አትበል በማለት የነቢይነትን ገድል አሸከመው እንደዚሁም ብዙዎች ጐልማሳነትንና ታናሽነትን ምክንያት በማድረግ ቤተክርስቲያንን ይርቋታል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍ "ጎበዞችም እንዲሁ ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው ብሎ ያስመክረናል ። ቲቶ 2፡6 ጳውሎስ ለጢሞቴዎስም "በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው" ማለቱ መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎዋልና ለጢሞቴዎስ ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ሁሉ በመሆኑ ለእኛም ደግሞ ነው ። ወጣትነት እንደ ጥላ ያልፋልና ። ከአበው ልሳን ሲነገር የወጣትነት ዕድሜ የእሳት ጊዜ በመሆኑ በእርግጥ እሳትነቱ ሐቅ ነው ሰሎሞን በምሳሌው ከጐበዛዝት ምክር የጐደለውን ብላቴና ተመለከትሁ ይላል ምሳሌ 7፡7 ስለዚህ የእሳት ጊዜ ተብሎ በአበው መነገሩ ጥበብ የተሞላ አነጋገር ነው በእርግጥ ምንም እንኳ ሥጋና ነፍስ ተደብለው የሚኖሩ ቢሆኑም ሥጋ ጊዜ ያዊት መሆንዋ "አሉ" አያሰኝም ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማይለወጥ ነው ልጅ አዋቂ ሴት ወንድ ብሎ አይለይም ቢሆንም እግዚአብሔርን ለማወቅና አውቆም ለመከተል ከዚህ ከወጣትነትና ከጉብዝና ወራት የበለጠ ምቹ ጊዜ



አይኖረንም ነቢያት ካህናት ሐዋርያትና ቅዱሳን ሁሉ ስንመለከታቸው ሁሉም የልጅነት የሕፃንነት የጉብዝናና የጐልማሳነት ዕድሜያቸውን ለእግዚአብሔር እንደሰጡና በአካሄዳቸው ሁሉ ለፈጣሪ መገዛታቸውን በዚህም የማያልፍ የጽድቅ አክሊል እንደተቀዳጁ እናያለን ። ጎልማሳነት የኃጢአት ምክንያት መሆን የለበትም ሳምሶን ውድቀት ሊያገኝ የቻለው በጎልማሳነት ስሜት ከእግዚአብሔር ይልቅ ደሊላን በማስቀደሙ ነው ፤ ለፈጣሪው ከመታዘዝ ይልቅ ለርስዋ ስለታዘዘ ነው ። ግን ትርፉ ኃጢአት ነው ኃጢአትም ከእግዚአብሔር ይለያል ጳውሎስ ስለዚህ ነገር ጢሞቴዎስን ሲያስጠነቅቅ "ክክፉ የጐልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ በንጹህም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል" ብሎታል 2 ጢሞ 2፡22 ቀጠል ያደርግና በቶሎ ወደእኔ እንድትመጣ ትጋደዒማስ የአሁኑን ዓለም ወደ ትቶኛል ሲል ለክፉ የጎልማሳነት ምኞት እጁን ስለሰጠ ስለዴማስ ይናገራል 2 ጢሞ 4፡10 ።

ስለዚህ የጎልማሳነት ጊዜያትን ከእግዚአብሔር ጋር በቤተክርስቲያን ፍቅር ብናሳልፍ ልጄ ሆይ በየዋህነትህ ሰውነትህን (ነፍስህን) ደስ አሰኛት የተቻለህንም ያህል አዘጋጃት ሲራ 10 28 የሚለውን መቀበል ይሆንልናል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ ትወደኛለህን ብሎ ሲጠይቀው ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ አዎን ጌታ ሆይ ሲል ጌታም በመጀመሪያ ጊዜ ግልገሎቼን አሰማራ በሁለተኛው ጊዜ ጠቦቶቼን ጠብቅ ፤ በሦስተኛው ጊዜ በጎቼን ጠብቅ ብሎታል ይህም የሚያሳየን ከወጣትነታችን ጊዜ ጀምሮ አምላካችንን መከተል እንዳለብን ሲያሳየን ነው ። በተጨማሪም በዚሁ ጌታ ኢየሱስ "አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል" ዮሐ 21፡15-18 ይህም እላይ ከጠቀስሁት ተመሳሳይ ይመስለኛል ። የአበባነት ጊዜያችንን ከክርስቶስ ጋር እንዲሆን አማራጭ የሌለው ውሳኔ ነው ትናንት የነበረው ዛሬ አለመኖሩ ዛሬ ያለውም ለነገ እንዲሁ እንደሆነ ያሳልና የመዳን ቀን አሁን ነው ። ወላጆችም አብርሃም ልጁን ለመሥዋዕት እንዲያቀርብ ተጠይቆ እንዳቀረበ እኛም ልጆቻችንን ለቤተ ክርስቲያን እናቅርብላት ቤተ ክርስቲያንም (እሷም) እግዚአብሔርን መፍራት ታስተምራቸዋለች ዳዊት" አንተ ልጄ ሰሎሞን ሆይ የአባትህን አምላክ ዕወቅ በፍጹም ልብህ በመውደድ አገልግለው "ዜና መዋዕል ቀዳ 28፡9 በማለት ለልጁ አምላኩን እንዳወረሰ ወላጆችም እንዲሁ ለልጆቻችን አምላካችንና ቤተክርስቲያንን እና ውርሳቸው ዮሐንስ ም "ጐበዞች ሆይ ብርቱዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውን ስለአሸነፋችሁ እጽፍላችኋለሁ" ብሎ ጽፎልናል 1ዮሐ 2፡12-14 ስለሆነም እኛ ጐበዞችና ወጣቶችም ፍጹም ታዛዥ በመሆን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት እንታነፅ የምናደንቃቸው ሐዋርያት ሊደነቁ የቻሉት ክርስቶስን ብቻ በመከተል መዳንን አገኙ እኛም እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሳችንን እናስለምድ ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁኑና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል ከሁሉም በላይ ለሆነው ክርስቶስ ሕይወታችንን እንስጠው ሰው ለመሆን በአምሳሉ የፈጠረንን አምላክ እንምሰለው እናታችን ቤተክርስቲያንን እንቅረባት በክንፎቿ እቅፉ ከሁሉ በኖህ ጊዜ እንኖህ በመርከቢቱ እንደዳኑ ታድነናለችና ጐበዝ ሆይ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ "የድሮውን ዘመን አስብ ትውልድንም ሁሉ አስተውል አባትህን ጠይቅ ይነግርህማል ሽማግሌዎችንም ጠይቅ ያስታውቁህማል" ዘዳ 32፡7 ።

ግርማይ ኃይሉ

## ምስጋና

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 18 እና በዚህ እትም ላይ «ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ» በሚለው ርእስ የወጡትን ጥንታውያን ፎቶግራፎች የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ስለ ፈቀደልን ፤ ወደፊትም ትብብሩ እንደማይለየን ሙሉ ተስፋ ስለሰጠን እጅግ እናመሰግናለን ።




www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን

## የአለቃ ጎሩይ ፈንታ ዜና ሕይወት

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ዜና መግለጫ በሆነው በዚህ ዓምድ ላይ የሚያውቃቸው እንዲያስታውሳቸው የማያውቃቸው በታሪካቸው እንዲተዋወቃቸው የሥመ ጥሩውን ኢትዮጵያዊ ሊቅ የአለቃ ጎሩይ ፈንታን ዜና እንገልጻለን ።

አለቃ ጎሩይ ፈንታ በጉንደር ክፍለ ሀገር ቤተ ልሔም በሚባለው ቦታ ከሊቀ ካህናት ፈንታና ከወይዘሮ ብሪቱ በ1855 ዓ.ም. መስከረም 16 ቀን ተወለዱ ።



ስመ ጥሩ ሊቀ አለቃ ጎሩይ ፈንታ

ወላጅ አባታቸው ገና በሕፃንነት ዕድሜ ሳሉ በሞት ስለተለዩዋቸው እናታቸው በመልካም ይዞታ አሳድገው ዕድሜያቸው ሲፈቅድ ከትምህርት ቤት አግብተዋቸዋል ።

ለትምህርት የነበራቸው ስጦታና ዝንባሌያቸው ።

አለቃ ጎሩይ ፈንታ ትምህርትን በመከታተልና ፈጥኖ በመቀበል ረገድ ልዩ የሆነ የተፈጥሮ ስጦታ ስለነበራቸው ከንባብ እስከ ዜማ ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ዐውቀው የሚወድቅ የሚነሣውን ፤ የሚጠብቅ የሚላላውን ጠብቀው ዘርፍ ከባለቤት አገናዝበው መጻሕፍትን ሲያነቡ ያዩዋቸው እጨጌ ቴዎፍሎስ ይህ ዕድሜ ይስጠው እንጂ ሊቅ ከሚያሰኘው ከከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የሚደርስ ነው ብለው ትንቢት ተናግረውላቸዋል ።

### እጨጌ ቴዎፍሎስ በትንቢታቸው ብቻ አል ተወሰኑም ።

በትምህርት ከከፍተኛው የሊቅነት ደረጃ እንደሚደርሱ ትንቢታቸውን ያስቀድሙላቸው እጨጌ ቴዎፍሎስ በምግብ በልብስ እንዲሁም በልዩ ልዩ ችግር ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ተሟልቶ እየተሰጣቸው አንድ ወገን ሆነው ትምህርታቸውን ብቻ እንዲከታተሉ ለአለቃ ጎሩይ የማያዳግም ትእዛዝ አስተላልፈውላቸዋል ፤ የመዝገብ ድጓ ምስክርም ከነበሩት ከመምህር ደርሶ ዜማ እንዲማሩ ከአደራ ጋር አስተዋውቀዋቸዋል ።

አለቃ ጎሩይ ፈንታ የፀዋትወ ዜማ እንዲሁም የመዝገብ ድጓ ትምህርታቸውን በዚሁ ትምህርት ቤት ከተከታተሉ በኋላ ፡

1ኛ/ በተድባበ ማርያም ከአለቃ ወረደ ቃል ዘንድ ቅኔ ተምረው ቢቀኙም ሞያውን ወይም ትምህርቱን በበለጠ ለማስፋፋትና አገባቡን ጠንቅቆ ለማወቅ በነበራቸው ፍላጐት መሠረት በጐጃም ክፍለ ሀገር አጋምኔ ቢሠውር ይባሉ ከነበሩት ምሥር ቅኔ ከነ አገባቡ ተምረው ለመምህርነት በቅተዋል፡

2ኛ/ የመዝገብ ድጓውን በሚገባ መላል ሰው ለማጥናት ስለአሰቡ እንደገና ወደትውልድ አገራቸው ተመልሰውና ተምረው ለመዝገብ ድጓ መምህርነት ተመርቀዋል ፤ የመዝገብ ድጓ አስተማሪያቸው መምህር ደርሶም በእግሬና በወንበሬ ተተክቶ የድጓ ምስክር ይሆናል እያሉ ቢያስቡም በልዩ ልዩ የትምህርት ፍቅር የተነደፈው የአለቃ ጎሩይ ፈንታ ልቡና በዜማና በቅኔ ሞያ ብቻ ሊወሰን አልፈቀደም ፤ ስለዚህም 3ኛ/ በጐጃም ክፍለ ሀገር ደብረ ጽላሎ ከተባለው ቦታ ከአለቃ እንግዳ የአርባ ስድስቱን መጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ ።

4ኛ/ በጐንደር ከታወቁት ከስመ ጥሩው መምህር ከወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ትርጓሜ ሐዲሳትን ፤

5ኛ/ አእምሮ ከተባሉትና እጅግ ከተመሰገኑት አስተማሪ የጐንደርን አቋቋም፤

6ኛ/ መዝሙር ካሣ ከሚባሉት የጐንደሩ ሊቅና በደብረ በግዕ ይገኙ ከነበሩት ከአለቃ ወልደ ማርያም የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ በሚገባ አድርገው ተምረው በሁሉም ሞያ ለመምህርነት በቅተዋል ።

### በፀዋትወ ዜማና በአቋቋም የነበራቸው ስጦታ

እንደእውነቱ ከሆነ የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት አቋማቸውን ከሚያጠናክሩ ሊቃውንት አንዳንዶቹ በዜማ ትምህርት ረገድ ያላቸው ስሜት እጅግ የሚደነቅ ባይሆንም ከትርጓሜው መጻሕፍት ሊቅነታቸው ጋር የመዝገብ ድጓና የአቋቋም መምህር የነበሩት አለቃ ጎሩይ በየአድባራቱና በየገዳማቱ በቅኔ ማኅሌት እየተገኙ ዚቅ ሲያወርዱ ፤ አመላለሱን ሲመልሱ ሲያመረግዱ ሲዘሙ በዜማ የታሸውና ቀድሞውኑ በተፈጥሮ የተዋበው ድምፃቸው የሰሚን ኅሊና ይማርክ እንደነበረ ይነገርላቸዋል ።

### አለቃ ጎሩይ አእምሮዋቸውን በምርምርና ታሪካዊ ቦታን በመጐብኘት አስፋፍተውታል ።

በዜማ በቅኔ በትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት የታነፀው የሊቁ የአለቃ ጎሩይ ፈንታ ህሊና ወደልዩ ልዩ የመጻሕፍት ምርምር ፤ እንዲሁም በታሪክ በባህል የተዋቡ ቦታዎችን ወደመጐብኘት ስላዘነበለ ስለብሉያት ቀጥተኛ ንባብና የአንድም ትርጓሜ ከነመምህር ሰው አገኘሁ ከነመምህር ፀበሉ ከነአለቃ ገብረኤልያስ ፤ ስለመጻሕፍተ ሊቃውንትም ከነአለቃ ተስፋ ከነሊቀጠበብት ወልደ ሥላሴ ፤ ከነ መልአከ ሰላም ገብረማርያም ፤ ከነመምህር እንግዳእሸት ተመካከረዋል ፤ ከዚህም ቀጥሎ ከብሉያትና ከሐዲሳት ስለአልተቆጠሩት አዋልድ መጻሕፍት (አፓክሪፍ) ዝርዝር ጥናት ለመውሰድ ፤ የባህልና የታሪክ ዕቃዎችን ለማየት በዘጌ በክብራን ፤ በጣና ቂርቆስ እየተዘዋወሩ የረጅም ጊዜ ጉብኝት አድርገዋል ፤ በዚ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# የሃይማኖት ዐምድ

> «ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

## የእግዚአብሔር ጠባይዕ

### ፫ኛ ዘለዓለማዊ ስለመሆኑ

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ከዳዊት መዝሙር በመጥቀስ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት ሲገልጥ እንዲህ ብሏል።

"ጌታ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ፤ ሰማያትም የእጅህ ሥራዎች ናቸው ። እነርሱም ያልፋሉ ፤ አንተ ግን ለዘለዓለሙ ጸንተህ ትኖራለህ ። ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደመጐናጸፊያ ትጠቀልላቸዋለህ ፤ ይለወጣሉም ፤ አንተ ግን ምን ጊዜም አንተ ነህ ፤ ዘመናትህም ከቶ አያልቁም ። (ዕብ 1 ፡ 10 - 12)

ዮሐንስም በራእዩ 22 ፡ 13 - 14 "እኔ አልፋና ኦሜጋ የመጀመሪያውና የመጨረሻውም ነኝ" አለ እግዚአብሔር በማለት ዘለዓለማዊነቱን ገልጧል ይህም ማለት "እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ነበር ፤ ከዘመናትም በኋላ ይኖራል።አያረጅም አያፈጅም አይለወጥም ፤ አይናወጥም በመንግሥቱ ሽረት በባሕርዩ ሞት የለበትም ። ለአስገኝነቱም ምክንያት አልነበረውም ፤ ቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ፤ ዛሬም አለ ፡ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው ።

የኢ.ት.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ገጽ 34 ፡

### 4ኛ ሁሉን አዋቂ የመሆኑ ጠባይዕ

እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል በሁሉ የሚገኝ ዘለዓለማዊ የመሆኑን ኑን ያህል ሁሉን ነገር የሚያውቅ በሰው ልቡና የሚጠልቅ የባሕርይ አምላክ መሆኑ ተጽፎአል ። የማይታየውን (የረቀቀውን) የነበረውንና ያለውን ወደፊትም የሚሆነውን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው ።

አስረጅ 1/ዳዊት በመዝሙሩ "አቤቱ አንተ አካሄዴን ሁሉ ፈጽመህ አወቅህ ፤ አንተ የማታውቀው ምንም ዓይነት ነገር በአንደበቴ የለም" ብሏል ።

2/ በዮሐንስ ወንጌል 2.24-25 "ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ስለነበር ስለ ሰው ማንም ሊመሰክርለት አይፈልግም ነበር ፤ ደግሞም ማንኛቸውንም አያምናቸውም ነበር ።

ምክንያቱም እርሱ ራሱ በሰው ልቡና ያለውን ነገር ሁሉ ያውቅ ነበርና ነው። የሚል ማስረጃ በግልጥ ሠፍሮ ይገኛል።

3/ በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 16 ፡ 7 "እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው።የኤልያብን መልክ ቀናነትና የቁመቱን ርዝመት አትይ ፤ እግዚአብሔር የሚያየው ሰው በሚያየው ዓይነት አይደለም።ስለዚህምንቁዋለሁ ፤ ሰው ፊትን ያያል ፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" ተብሎ ተጽፎአል ።

ስለዚህምነው በዮሐ.1፡3"ሁሉ በርሱ ሆነ ፤ ያለርሱ ወይም እርሱ ሳያውቀው ግን ምንም ምን የሆነ ነገር የለም" ተብሎ የተነገረው 4ኛ ስለ ጠቢብነቱ በመዝሙር ሁሉን በጥበብ ፈጠርክ" የሚለውን ቃል ማስታወስ ይበቃል ።

### 5ኛ/ ቅዱስና ፍጹም የመሆኑ ጠባይ

እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ክፋት የሌለበት የበደል ሥራ (ኃጢአት) ሁሉ የማይስማማው ቸር መሐሪና ርኅሩኅ ነው ። ስለዚህም ""እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም እንዲሁ ቅዱሳን ሁኑ" ሲል አዘዘ ። (ዘሌ. 19.2) መላእክትም "ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍጹም" እያሉ ያመሰግኑታል ። (ኢ.ሳ. 6.3)።

ሰውን ንጹሕ ነው ቅዱስ ነው ብንለው በየትም ዞሮ ከኃጢአት (ከበደል) አይነፃም ። ብዙ ድካመትም አለበት እግዚአብሔር ግን ድካመት የሌለበት ኃያል በመሆኑ ንጹሕነቱና ቅዱስነቱ ፍጹም ነው።

### 6ኛ/ ትክክለኛ ፈራጅ ስለመሆኑ

እግዚአብሔር ፍጹምና ቅዱስ አምላክ ነው ። ስለዚህም በማንም ላይ በግብዝነት ወይም በሐሰት አይፈርድም ስለዚህም ሕግ አፍራሾችን ያለምንም አድልዎ ይፈርድባቸዋል ይቀጣቸዋልም ሕግ ፈጻሚዎችንም ይፈርድላቸዋል ። ድሃውንና ችግረኛውን አይንቅም ሀብታምን በሀብቱ ፤ ኃያሉን በጉልበቱና በሥልጣኑ አይፈራም ስለዚህም ነበር ሐዋርያው ጴጥሮስ በሐዋ. 10.35 "በዕውነት አስተዋልሁ እግዚአብሔር የሰው ፊት አይቶ አያዳላም" ሲል የተናገረው ።

በ2ኛ ዜና መዋዕል 19 ፤ 6-7" ፈራጆች ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው ብቻ እንደማትፈርዱ ዕወቁ ፡ እርሱ በፍርድ ጊዜ ከናንተ ጋር ነው ። የምታደርጉትን ተመልከቱ ፤ አሁንም እግዚአብሔርን መፍራት በናንተ ላይ ይሁን ፤ በአምላካችንም በእግዚአብሔር ዘንድ በደልና ለሰው ፊት የማድላት ነገር የለም ። መማለጃ በመቀበልም ፍርድን ማዘንበል አይገባንምና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" የሚል የጽሑፍ ማስረጃ አለ ።

ስለዚህ ፍርድ የእግዚአብሔር ስለሆነ ፈራጆች በትክክል ሊፈርዱ ይገባል ።

እግዚአብሔር በባህርዩ ሁሉን ያውቃልና ።

ቁ/ መክብብ አትናው




www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

በመላዋ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ጥንታውያንና ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል በደሴተ ጣናና በአካባቢዋ የሚገኙት ገዳማትና አድባራት ናቸው ።

የጣና ሐይቅ የሚገኘው በሰሜን ኢትዮጵያ በጉጃምና በጎንደር ክፍለ ሀገር መካከል የሚገኝ በሌላው ክፍለ ሀገራት ከሚገኙ ሐይቆች ባሕሮች በስፋትም ሆነ በጥልቀት መጀመሪያውን ደረጃ ይዞ የሚገኝ ሲሆን በዓለም ከታወቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ወንዝ የአባይ ምንጭ ነው ።

የጣና ሐይቅ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ዋና መሥሪያ ቤቱ ባሕር ዳር ከተማ የሆነ ናሺጋ ጣና የተባለ የባሕር ትራንስፖርት ድርጅት ስለአለ መጠነኛ የሆኑ የሞተር ጀልባዎች አዘጋጅቶ ከባሕር ዳር ዘጌ ፣ ደቅ ፣ ጉርጉራ ፣ ቁንዝላ ፣ ደልጌ ከተባሉ ሥፍራዎች ሰውም ሆነ ማንኛውም የንግድ ዕቃና ጥራ ጥሬ በባሕሩ ላይ በማጓጓዝ ከፍ ያለ አገልግሎት ይሰጣል ።



ባለ አራት ማዕዘን (ባስሊካ) የጣና ቂርቆስ ቤ. ክርስቲያን

የጣና ባሕር አካባቢ በሙሉ እጅግ በጣም ለም መሬት ከመሆኑ የተነሣ ለከብት ርባታም ሆነ ለማንኛውም የእርሻ ሰብል በጣም ተስማሚ የሆነ የአየር ጠባይ ስለአለው ደንብያ ፣ ፎገራ ፣ አለፋ ጣቁሳ ፣ አቸፈር ፣ ባሕር ዳርና ዘጌ ከተባሉት ሥፍራዎች የሚኖሩ ኅብረተሰቦች በሙሉ ግሩም በሆነ ሁኔታ ከብት የሚያረቡና ጤፍ ፣ ማሽላ ፣ ሽንብራ ፣ ኑግና ሱፍ በማምረት የሚኖሩ በጣም ሀብታም የሆኑ ገበሬዎች ናቸው ይህም በመሆኑ ወደእነዚህ አካባቢ የሄደ ማንኛውም ሰው መስተንግዶው ፤ ወተት ፣ እርጎ ፣ እንጀራ በአይብ ፣ ተፈትፍቶ ይሰጠዋል ። ከወተቱ ብዛት የተነሣም እንኳንስ ሰው ይቅርና አንቱ ተፈልቶ አይቡ ከወጣ በኋላ አንቱ በገንዳ ተደርጎ ለከብቶች ይሰጣል ። የጣና ሐይቅ ዳሩም ሆነ ውስጡ በተፈጥሮ ፀጋ የታደለ በመሆኑ ውስጡን ቢዳስሱት ዓሣ እንጂ አሸዋ የማይገኝበት ሐይቅ ነው ።

የጣና ባሕር በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በሰው ሠራሽ ነገርም ጥሩ በመሆኑ በውስጡ በሚገኙ ደሴቶችና አካባቢው ቅዱሳት ገዳማትና አድባራት ይገኛሉ ።
እነርሱም በደሴተ ጣና ውስጥ ፦

1/ ዳጋ እስጢፋኖስ 2ኛ/ ናርጋ ሥላሴ ፣ 3ኛ/ ደቅ አርሴማ ፣ 4ኛ/ ክብራን ገብርኤል 5ኛ/ ገሊላ አቡነ ዘካርያስ ፣ 6/ እንኳራ ተክለሃይማኖት ናቸው ከላይ ከጠቀስኳቸው ገዳማት ሌላ በጣና ባሕር አካባቢ የሚገኙ በጣም ጥንታውያን የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ 1ኛ/ ጣና ቂርቆስ ፣ 2ኛ/ ክርስቶስ ሠምራ ፣ 3ኛ/ ምጥሌ ፋሲለደስ ፣ 4ኛ/ ጉርጉራ ደብረሲና ማርያም ፣ 5ኛ/ መንዳባ አቡነ አሳይ ፣ 6ኛ/ በዘጌ ውስጥ ውራ ኪዳነ ምህረት ፣ አባ በትረ ማርያም ዩጋንዳ ተክለ ሃይማኖት ባሕር ዳር ጊዮርጊስ የሚባሉ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት ናቸው ከዚህ ሌላ በጣም ጥንታዊነት የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት በጣና ባሕር አካባቢ በብዛት ይገኛሉ ። ከላይ ስማቸው በዝርዝር የተገለጹት ገዳማትና አድባራት ግን ከግራኝ መሐመድ ወረራ በፊት የተተከሉና የገዳም ማኅበራዊ ኑሮ የተመሠረተባቸው ብዙ ሰባኪያን ወንጌል የወጡባቸው የልዩ ልዩ ቅዱሳን አፅም ያረፈባቸው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ቅዱሳት ገዳማትና አድባራት በመሆናቸውና በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በዓለም ታሪክ ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ ይዘው የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ቅርሳ ቅርሶች በብዛት ተከማችተው የሚገኙባቸው ስለሆኑና ለአገራችን ከፍተኛ የሆነ የቱሪዝም ገቢ የሚያስገኙ በመሆናቸው ከሌሎቹ ለይቼ በማቅረብ እንደባሕር ውሃ ተቀድቶ ከማያልቀው ታሪካቸው የማውቀውን ያህል በጭልፋ ጨልፌ ለአንባብያን አቀርባለሁ ።

ያለ አባት ልጅ አይወለድምና የነዚህ ጥንታዊያን ገዳማትና አድባራት ወላጅ አባት ስለሆነውና ለእነዚህ ቅዱሳት ሥፍራዎች መመሥረትና መስፋት ምክንያት ስለሆነው ስለጣና ቂርቆስ ከቦታው ድረስ በመሄድ ያገኘሁትንና ያጋጠሙኝን ሁሉ ለአንባብያን ባቀርብ ደስ ይለኛል ።

1/ በተቀጣጠሉ ብራናዎች የነቢያት ፣ የሐዋርያት ፣ የጻድቃን ፣ የሰማዕታት ሥዕል የተሳለበት የሚዘረጋና የሚተጣጠፍ በጥንታዊ የሐረግ አሣሣል ያሸበረቀ ሥዕለ አድኅኖ

2/ በየተአምሩ ሥዕል ያላት ተአምረ ማርያም

3/ በጣም ጥንታዊ የሆነ የመዳብ መስቀል

4/ ሁለት በጣም ጥንታውያን የሆኑ በትረ መስቀሎች



በጣና ቂርቆስ የሚገኝ ጥንታዊ የመዳብ መስቀል

5/ መጠነኛ የሆኑ ሥዕለ አድኅኖች

6/ በጎንደር ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ አካባቢ የተሳለ ፍትሐነገሥት

7/ የዜማው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በእጁ የጻፈው ነው እየተባለ የሚነገርለት የዜማው ምልክት የሌለው ድጓ

8/ በየዕለተ ሰንበቱና በየወር በዓላቱ የሚገለገሉባቸው ጥቂት መጻሕፍትና አልባሳት በቄሰ ገበዙ አማካይነት ወጥተውልኝ በዓይኔ አይቼ ፎቶግራፍ ለማንሳት ችያለሁ ።

1ኛ/ ከላይ በጠቀስኳቸው መጻሕፍቶች መካከል በአጭሩ ሳልገልፀው የማላልፈው ጉዳይ አለ ይኸም በቅዱስ ያሬድ እጅ ተጻፈ ስለሚባለው ድጓ ነው ። በታሪክ እንደሚታወቀው ሁሉ ቅዱስ ያሬድ የነበረው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው የጣና ቂርቆስ ገዳም ግን የተመሠረተው በአፄ ሀምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በተባሉ ጻድቅ ለመሆኑ ዶክተር ታደሰ ተአምራት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ፕሮፌሰር ቸርች ኤንድስቴት በተባለው መጽሐፋቸው በሚገባ ገልፀውታል ። የዚህ መጽሐፈ ድጓ ሥነ ጽሁፍም ሆነ የብራናው ጠቅላላ ይዘት በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተጻፉት መጻሕፍት ምንም ዓይነት ልዩነት የለውም ነገር ግን ምልክት የሌለው በመሆኑ የያሬድ ድጓ ሊሆን አይችልም እውነቱ ግን የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደሚተርኩት የቀድሞ ድጓ ምልክት አልነበረውም ለሚባለው ታሪክ የጣና ቂርቆስ ድጓ እንደምስክርነት ሊቀርብ ይችላል ።

2ኛ/ እዚያው በሰነበትኩበት ሰሞን ቤተ ክርስቲያንና አካባቢውን እየተዘዋወርኩኝ እመለከት ነበር ስለዚህ ቤተክርስቲያኑ የሣር ክዳን ያለው በአራት መዓዝን በተቀረፀ በጥርብ ድንጋይ የተገነባ ሲሆን በተለይ የቤተ መቅደሱ ህንፃ ግን ቀይ ሸክላ በመሳሰሉት ድንጋዮች የታነፀው በዚያ ዓይነት ድንጋይ በጣና ቂርቆስ አካባቢ አይገኝም ነገር ግን ከየት እንደመጣ ብጠይቅ የሚያስረዳኝ ሰው አላገኘሁም ከቤተ ክርስቲያኑ በስተደቡብ በኩል አንድ አለት አለ በዚህ አለት ላይ ሁለት መጠነኛ የሆኑ ከአለት የተፈለፈሉ ጉድጓዶች አሉ ። እነዚህ ጉድጓዶች የቀይና የጥቁር ቀለም መበጥበጫና ማቡኪያ ነበሩ ብለው ተርከውልኛል ።

4ኛ/ በዚህ አካባቢ በአለት ላይ የተተከለች በጣም ጥንታዊት የሆነች የብረት መስቀል አለች ካህናቱ እንደሚሉት ከሆነ ይህ መስቀል የአቡነ ሰላማ ነበር ይላሉ ። ይህ መስቀል በዘመናችን አንድ ተአምር ፈጽሞአል ተአምሩም አንድ መነኩሴ ከትግራይ ክፍለ ሀገር ወደጣና ቂርቆስ ይመጣና ይቀመጣል በዚህ ጊዜ ይህ መስቀል የአቡነ ሰላማ ነው የሚል ታሪክ ከካህናቱ ይሰማል እንግዲያማ አባ ሰላማ አገራቸው ትግሬ ነው ስለዚህ ይህን መስቀል እዚህ ማን አመጣው ይልና በሌሊት ሰርቆ ይጠፋል ። ነገር ግን መነኩሴው ይህን መስቀል ይዞ ሃገር ለሀገር ሲንከራተት ከኖረ በኋላ በዓመቱ ይዞት ወደ ጣና ቂርቆስ መጣና በሕዝቡ ፊት ቆሞ እንዲህ ሲል ተናገረ ይህን መስቀል ከወሰድኩበት ቀን ጀምሮ የቀን ዕረፍትና የሌሊት እንቅልፍ አላገኘሁም እንዲያውም ሌሊት በሕልሜ አንድ ሰው እየመጣ ይህን መስቀል ካመጣህበት መልስ እያለ ስለአስቸገረኝ ይዤው መጥቻለሁ ሲል በሕዝብ ፊት ተናዝዞአል በአሁኑ ጊዜ መስቀሉ በቦታው ይገኛል ።

5ኛ/ ከዚህ ሌላ ከጣና ቂርቆስ በስተሰሜን አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ከባሕሩ ጫፍ ላይ ኃጢአተኛና ጻድቅ የሚለይባትናት የምትባል ቀዳዳ ድንጋይ አለች ። ይህችን ቀዳዳ ድንጋይ ሾልኮ ያለፈ ሰው ፍጹም ጻድቅ ነው ተብሎ የሚታመንበት ሲሆን ቀዳዳዋን ሳይሾልክ የቀረ ሰው ግን እንደ ኃጢአተኛ ይቆጠራል ከዚህም እምነት የተነሣ በቂርቆስ ዓመት በዓልና በግንቦት 12 ቀን የክርስቶስ ሠምራን በዓል ለማክበር የመ





www.ethiopianorthodox.org

# እውነተኛ ፍቅር

የተለያዩ ሰዎች ፍቅርን ልዩ ልዩ ትርጉም ይሰጡታል ። ለብዙዎች በተለይም በዚህ ዘመን የፍቅር ትርጉም በፆታ ልዩ የሆኑ ሰዎች በሚያደርጉት ግንኙነት የሚወሰን ነው ። በዚህ አመለካከት የፍቅር ጥልቀቱና ምጥቀቱ ፤ አበድኩልሽ ሞትሁልሽ ወይም አበድሁልህ ሞትሁልህ እስከ ግብረ-ሥጋ ድረስ ነው ። እንዲህም ሲባል ሁሉም ለጋብቻ አይበቃም ማለት አይደለም ፤ ብዙኃኑ ሲታዩ ነው እንጂ ። ፍቅርን በዚህ አመለካከት ተቀብለው ፤ ርምጃ ጀምረው ፤ ይሆነኝ ትሆነኛለህ ተባብለው ለጋብቻ በቅተው የቤተሰብ ድንጉርጉር በሳምንቱ ፤ በወሩ ግፋም ቢል በዓመቱ ያልደረሰባቸው በጣም አነስተኞች ናቸው ። ምክንያቱም ፍቅሩ በመልክ ማለትም በውበቱ በውበቷ ላይ ብቻ የተመሠረተ ስለሚሆን ነው ። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ዓይነቱ ፍቅር ከእግዚአብሔር አምልኮ የራቁ ፤ በክህደት ባሕር የተጠመቁ ወይም የአምልኮት መልክ ኖሯቸው ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ሰዎች የተለማመዱት ፤ የሚለማመዱት ነው ።

በቤተሰብ ደረጃ የሚታይ ፍቅርም አለ ። እናት ዘጠኝ ወር አርግዛ አምጣ የወለደችውን (ቻትን) የሥጋዋን ቁራጭ ልጅዋን ትወደዋለች (ታለች) ። ባሏም የኑሮ ጓደኛዋ ፤ የችግሯ ተካፋይ ፤ በሥጋ ደረጃ ከእናት ከአባቷ ይልቅ በቅርብ የምታገኘው አጋሯዋ በመሆኑ በእርሱ ትምክህት አላት ። በአንፃሩም አባት ልጁንና ሚስቱን ይወዳል ። በቤተሰቡ ውስጥ ባለመግባባት ፤ ባለመጣጣም ምክንያት ከሚነሣው አምባጓሮ በስተቀር እርስ በርስ መተሳሰብ ፤ መዋደድ አብዛኛውን ጊዜ ይታያል ፤ ይህ ዓይነቱ መዋደድ (መፋቀር) ሰማያዊት መንግሥትን በሚጠባበቁ በክርስቶስ አማንያንና ምንም እንኳ በእግዚአብሔር እምነት ባይኖራቸው በሞራል በጸኑ ቤተሰቦች ሁሉ ይታያል ። በኑሮዋቸው መጣጣም የሌላቸው ባልና ሚስት ሁል ጊዜ ከመነታረክና በትር ከመማዘዝ ብሎም ከመፋታት በስተቀር ፍቅር ላይኖራቸው ይችላል ።

ሰው ሁሉ ባልንጀራውን (በግብሩ የሚመስለውን) ይወዳል ። ፍቅሩ ግን ዘላቂነት ያለው ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ።

እውነተኛ ፍቅር ክርስቶስን ያስቀድማል ፤ ምክንያቱም ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያው መልእክቱ “ ... እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ።” 4 ፡ 8 ብሎ እንደጻፈ የፍቅርን መሠረት ራሱን ፍቅርን (እግዚአብሔርን) በቅድሚያ ማወቅና መረዳት ስለሚያስፈልግ ነው ። እግዚአብሔርን የሚያውቅ በፍጹም ልቡ ፤ በፍጹም ነፍሱ የሚያመልክ ሰው የሥጋውን ምኞት የሚቆጣጠር ፤ በአሸብራቂዋ ዓለም ከመጉምጀት ራሱን የሚገታ መሆን ይገባዋል ። በዚህም ለነገር ሁሉ ታጋሽ ይሆናል ። ብዙዎች በቀላሉ በሚታለሉበት በከንፈር ወዳጅነት ማለትም ሥር-አልባ በሆነ የሥጋን ላምሮት ለማርካት በሚደረገው “ፍቅር” አይነደፍም ። ከዚህ ይልቅ ከሁሉም የሚበልጠውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ያከብራል ። በዚህ አባባል እውነተኛው ፍቅር ከዓለማውያን “ፍቅር” የተለየ ነው ። በእውነትም ነው ። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለእውነተኛው ፍቅር ጽፏል ። “በእርሱ በኩልበሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና ። ፍቅርም እንደዚህ ነው ፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጅ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድ ነው አይደለም ።“ 1ዮሐ.4 ፡ 10 ሲል ፍቅር ራስን ለወዳጆቹ ቀርቶ በደልን ለፈጸሙበት እንኳ አሳልፎ እስከመስጠት የጠለቀ ነው ። ሕያው ክርስቶስን ስንበድለውና ስናሳዝነው በማሳዘናችንና በመበደላችን ኋላ የሚደርስብንን መሪር ሐዘን ተመልክቶ ቅንጣት በደል ሳይኖርበት ስለእኛ ሥጋን ለብሶ በምድር ላይ ተመላለሷል ፤ እስከሞት ወዶናል ። ፍቅር ይህ ነው ። ይህ ፍቅር አምላክ እርስ በራሳችን እንድንዋደድ ተናግሯል ። ስለዚህም ትእዛዙን ልንከተል ይገባናል ። እግዚአብሔርን የሚወድ ከእርሱ ተወልዷል ፤ እግዚአብሔርንም ያውቃል። እግዚአብሔርን ወደድሁ ለማለት በመጀመሪያ ደረጃ የምናየውን ወንድማችንን ስናፈቅር እንደሆነ በታላቁ መጽሐፍ ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኛለን ። የእርስ በእርስ መዋደድ ሳይኖር እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለት ግን እውነትነት የሌለው አፍአዊ ፤ እንዲያው ለይስሙላ የተባለ “ፍቅር” ነው ።

ፍቅርን (እውነተኛውን) መከታተል ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ተገቢ ነው።ከእምነትና ከተስፋ ብልጫ ያለው ፍቅር ነው። ጠላት ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል እየገባ መቃቃርን ሊያመጣ ይወዳል ። እርሱ ምንጊዜም አያርፍምና ፤ ለሞኞች ፡- “እግዚአብሔርን እመን ፤ እርሱንም ውደድ ጠላትህን ግን ጥላ” እያለ ይመክራል ። በዚህም የተሰናከሉ አማንያን ቁጥር በቀላል የሚገመት አይደለም።እነርሱም ከእውነተኛ ፍቅር የራቁ አልመሰላቸውም።ፍቅር ግን ይታገሳል ። (1ቆሮ. 13 ፡ 4)

አንድ አባት ስለክርስቶስ ሲመሰክሩ የፍቅርንም ጠቃሚነት ተናግረው ነበር ። ትምህረታቸውም “ፍቅር የሌለው ሃይማኖት አያጸድቅም” ብለዋል ። ጥላቻ ፤ ክፋት ፤ ተንኮል በሞሉበት ልብ እነዚሁ የክፋት ሥራዎች ተጠርገው እስካልወጡ ድረስ ለፍቅር ቦታ እንደማይሰጡ እሙን ነው ። ክርስቲያን ግን በአምላኩ ኃይል እነዚህን ደምስሶ ፍቅርን በመተካት እምነትንና መልካም ሥራን አዋሕዶ በመጽናት ጽድቅን ለማግኘት እንዲተጋ ይገባዋል ።

በአጠቃላይ አነጋገር ምንም እንኳ በተለያዩ ሰዎች ለፍቅር የተለያዩ ትርጉምና አመለካከት ቢሰጠውም እውነተኛው ፍቅር ራሱን ስለሰው ልጆች አሳልፎ የሰጠው ሕያው ክርስቶስ ነው።እርሱን ልናፈቅር ይገባናል ። እርሱ በእኛ መካከል እንዳለ የምናውቅ እርስ በርሳችን ስንዋደድ ነው።ክርስቲያኖች ሆይ በእውነተኛው ፍቅር እንመላለስ ። በስም “ፍቅር” ብለን የሥጋ ፈቃዳችንን በመፈጸም እንዳንጎዳ ማስተዋል ይኖርብናል ። 1ቆሮ. 13 ፡ 1 - መጨረሻና የመጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ብናነብብ ስለፍቅር በበለጠ ለመማር እንችላለን ።

ዐቢይ ይግዛው

---

ጣው ሕዝብ በጠቅላላ ይህችን ቀዳዳ ሳይሞክር አይሄድም የሾለኩት ሲደሰቱ ያልሾለኩት ደግሞ እየደጋገሙ ከድንጋይ ጋራ ሲታገሉ ይውላሉ ።

ጣና ቂርቆስ የቅዱሳት መጻሕፍትና የጥንታውያን ቅርሳ ቅርሶች መጋዘን ነው እየተባለ ቢነገርለትም ከቦታው ድረስ በመሄድ ያገኙሁት መልስ ከሩቅ ዋሻ ተቀብሬዋል የሚል መልስ ቢሰጠኝም ከመሬት በታች ያለውን ውሸት ሳይሆን ከመሬት በላይ ያለውን እውነት ተመልክቼ ቀዳዳዋን ድንጋይ ሾልኬ ተመልሼአለሁ ።

ይቀጥላል ።

ገርማ ኤልያስ



# የጤና ዐምድ

በሚኖረን የሕይወት ዘመናችን በሙሉ ጤንነት ለመኖር ሁላችን እንወዳለን ነገር ግን በሽታ ባልጠበቅነው መንገድ ሲመጣ የበሽታውን ዓይነትና የአመጣጡን ሁኔታ አውቀን እንዴት መከላከል እንደምንችል ሐኪሞችን ብናማክር ወይም የጤናን አጠባበቅ የሚጠቁሙትን መጻሕፍት ብንመለከት አሁን በጊዜያችን ብዙዎች የሚሰቃዩባቸውን በሽታ መንስኤያቸውንና መከላከያቸውን የጤናና የደስታ ጉዳና የተሰኘው መጽሐፍ ምን እንደሚል እንመልከት (እንጠቁማችኋለን) ።

ሁላችንም እንደምናውቀው ደስታ የሚገኝ በጤንነት እንጂ በሚኖረን ብዙ ነገሮች አይደለም የፍላጐታችን ነገርና ከዚያም በላይ የሆኑ ሁሉ ቢሰበሰቡ ጤንነታችን ከሌለ የምንደሰትበት የለም ። ይህ የታመነ መሆኑን የጤና ጉድለት ያለባቸው ሰዎች ቶሎ መመልከት ሲችሉ በሙሉ ጤንነት ውስጥ ያለን ደግሞ የጤናችንን ነገር ቸል እንለዋለን ። በአንድ በሽታ የተያዘን ሰው ሄደን ብንጠይቀው ወይም እራሱ ቢያሰላስል ትውስ የሚለው የጤንነቱ ጉዳይ ነው በጤንነቱ ጊዜ በጣም የሚያስደስተው ነገር በሕመም ላይ እያለ ቢቀርብለት ከመጤፍም አይቆጥረውም ።

አሁን ደግሞ ብዙዎችን የሚያጠቃቸውና የሚያስፈልጋቸውን ምግብ ቢሆን እስከመተው የሚያደርሳቸው እንዲሁም የሚያሰቃያቸው ብዙውን ጊዜ የጨጓራ በሽታ ወይም (የታፋቁስል) እየተባለ የሚታወቀው ነው ። የዚህ በሽታ መነሻው ሐኪሞችና የጤንነት መጻሕፍት እንደሚሉት መጨነቅ (ማሰብ) መርበትበት ነው ብዙውን ጊዜ በሽታው የሚያጠቃቸው የተማሩ ሰዎችንና ከባድ ኃላፊነት የተጣለባቸውን ሰዎች ነው ። ይህ የሚያመለክተው የበሽታው መነሾ እነዚሁ የተጠቀሱት ምክንያቶች መሆናቸውን ነው በሽታው ከያዘ በኋላ ጨጓራን ያቃጥላል ። ይኸም የሚሆነው ሆድ ባዶ በሚሆንበት ጊዜ ነው ።

መከላከያው ፡- በተወሰነ ጊዜ የተስተካከለ ምግብ መብላት ፤ ተገቢ ዕረፍት ማድረግና ሲጃራ አለማጨስ ሲሆን ከመጨነቅ ምክንያት በሽታው የሚመጣ ከሆነ በእግዚአብሔር መታመን ለልባችን ሰላም ስለሚሰጠን የጨጓራ በሽታ ሊያገኘን አይችልም ። ሐኪሞች በጨጓራ በሽታ የሚሰቃዩትን በተወሰነ ሰዓት እንዲበሉ ዕረፍት እንዲያደርጉና ማጨስ እንዲተዉ ይመክሩአቸዋል ።

የልብ ሕመም ሌላው አጥፊ በሽታ ደግሞ የልብ ሕመም ነው ልብ በሕይወት እስካለን ድረስ ሥራውን የማያቆም ፓምፕ ነው ስንተኛም ሆነ ስናርፍ ወይም ስንሠራ እርሱ ግን አያቆምም ሥራ ስንሠራ ካረፍንበት ወይም ከተኛንበት ጊዜ አብልጦ ይመታል ልብ ቢታመም ጠንቁ ለመላ የአካል ክፍሎቻችን ይተርፋል ። ልባችን ጤነኛ እንዲሆን ከፈለግን በደንብ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ሥራ መሥራት ለልብ ጤንነት አስጊ ነው የሚለው አነጋገር ትክክለኛ አባባል አይደለም ፤ በተወሰነ ጊዜ የሰውነት ማጠንከሪያ መሥራት ልብን ጤነኛ ያደርጋል ከዚህም የተነሳ ዕድሜያችን ሊረዝም ይችላል ።

ለልብ በሽታ ጠንቁ ሥራ መሥራት ሳይሆን ትንባሆ ማጤስ ነው የምንበላው የምግብ ዓይነት የዕድሜያችንን እርዝመትና የልባችንን ይዞታ ይወስናል ሐኪሞች መርምረው እንደደረሱበት ቅባት የበዛበትና ጣፋጭነት ያለው ምግብ የሚበሉ ሰዎች ከሌሎች የበለጠ የልብ በሽታ ያጠቃቸዋል እነዚህ የምግብ ዓይነቶች የደም ሥሮችን ያውኩና የልብ ድካምን ያስከትላሉ ፍራፍሬ ፤ ቅጠላ ቅጠል ጥራጥሬ የፍራፍሬ (የቅጠል) ቅባቶች የመሳሰሉ ቀላል የምግብ ዓይነቶች ዕድሜን ከመቀጠላቸውም ሌላ ልብን አይጐዱም ። ሌላው የክብደት ብዛት የብዙ በሽታ ዓይነቶች ጠንቅ ነው በተለይ ለልብ ሕመም አንደኛውና ዋናው ጠንቅ እሱ ነው ከመጠን በላይ ክብደት ያለን ከሆነ ምግባችንን ቀስ በቀስ በመቀነስ የልባችንን ጤንነት እንጠብቅ ።

የደም ማነስ (አኒምያ) ሌላውም አስቸጋሪና የብዙዎች በሽታ ሆኖ የተለመደው ይኸ ነው የደም ማነስ ማለት ያልተስተካከለ ወይም ዝቅተኛ ደም ማለት ነው ። የደም ሴሎቻችን ሲያልቁ አዲስ የደም ሴሎች መተካት ይኖርባቸዋል አዳዲሶቹ ደግሞ ሊተኩ የሚችሉት በተሟላ ምግብ አማካኝነት ነው ። የተሟላ ምግብ ካልተገኘ ያንጊዜ የደም ማነስ ይመጣል ። የደም ማነስ ባለቀት ሴሎች ምትክ አዲስ ሴሎችን ሊተካ የሚችል ምግብ ካለማግኘት ፤ በልዩ ልዩ ምክንያት አካል በቀላሉ ሊተካ የማይቻለው ደም ሲፈስ ከጠባ በሽታ ጠንቅና ከሆድ ትሎች ሊመጣ ይችላል ። የበሽታው ምልክት የሰውነት መድከምና መገርጣት ፤ የጣት ጥፍሮችና የዓይን ሥሮች መንፃት ነው እነዚህ ምልክቶች በሰውነታችን ከታዩ ወዲያው ወደ ሆስፒታል ሄዶ የሀኪም እርዳታ ማግኘት ያስፈልጋል ። መከላከያው ከአካላችን ደም ሲፈስ ወዲያ የሚያስቃዩ በሽታዎችን ተመልክተናል እንግዲህ እኛ በስህተት፣በድፍረትና በቅንጦት የምናደርጋቸው ያልተስተካከሉ ሁኔታዎችና ጤንነታችንን አለመጠበቃችን ለሚያሰቃየን በሽታ አሳልፎ እንደሚሰጠን ስንመለከት የጤናችን ሁኔታ በእጃችን እንዳለ እናውቃለን ።

ያለን አንድ ሕይወት ብቻ ነው በዚህ ባለን አንድ ሕይወት ዋጋ እንዲኖረን በሙሉ ጤንነት የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድንወርስ ለጤናችን አብዝተን ልንጠነቀቅ ይገባል የሌሎችን ሁኔታ በደንብ ለመጠበቅ ፤ ከራሳችን ጀምረን ሌሎችን ሥነፍጥረቶች ሁሉ ተመልክተን እግዚአብሔርን ለማመስገን እንድንችል ጤናችን መልካም ይዞታ እንዲኖረው ማድረግ ነው ።

ወይ. ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች

ኢትዮጵያውያን ከጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተመሠረተውን የኅብረትና የቅድስና ሕግ በትክክል የጠበቁና በሥራም ያሳዩ አባቶች ነበሩ ። አሁንም አሉን ። ስለዚህ የጥንታውያን አባቶችን መንፈሳዊ ሥራና መመሪያ የዛሬው ትውልድ አውቆ በበላም ለመኖር የሚረዳው አስተባባሪ ዓላማ ነው ። ይህም አሁን የምንመለከተውን ክፍል ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነታቸው አምነው የሚተባበሩ እንጂ በሀገሩ ስፋት ውስጥ በሚገኘው ልዩ ልዩ ቋንቋና በጐሣ በወንዝ ምክንያት ፈጽመው የማይለያዩ የቅድስና ተባባሪዎች በመሆናቸው ተባብረው የሚወስኑትን ገዳማዊ ሕግና ሥርዓት የጋራቸው በሆነው የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ እስከ ቅርብ ጊዜ በግዕዝ ነው ሲጽፉ የኖሩት ይህንም ስል በግዕዝ ቋንቋ ከመዘገቡት በየዘመኑ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ነው ። ሆኖም በመጠኑ ከግዕዙ ቃል ያለውን የሚያስረዳን በተቀደሱ ቦታዎች በየክፍሉ የሄዱ መናንያን የኅብረትን ጠቃሚነት አውቀውና ጠብቀው መጭውም ትውልድ እንዲጠብቅ ጽፈው የተመሩበትን ጥንታዊ መዝገበ አበው ከብዙ በጥቂቱ አመሠራረቱ እንዲህ ይላል ። በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያውያን የአንድነት ማኅበር ያቋቋሙበትን ዘመን የኢትዮጵያን መንፈሳዊ ተግባር በዓለም ላይ የተደነቀና የተመሰገነ ስለሆነ ቸሩሊ ከተባለው መጽሐፍ (ደራሲ) በብዙ ቋንቋዎች ስለ ኢትዮጵያውያን ቅድስና የሚያስረዳ ከተጻፈው ከሁለተኛው ክፍል (ማለት ከሁለተኛው መጽሐፍ) ከገጽ 380 - 496 ድረስ እጅግ በጣም ብዙ ማስረጃዎች በግዕዝ ቋንቋ ከተጻፉት የመጀመሪያውንና የአንድነት መሠረት የሆነውን አቀርባለሁ ይህም ከገጽ 380 እስከ ገጽ 381 ድረስ ያለውን በግዕዝ ከተጻፈ ቃል እንዲህ ብሎ ይጀምራል ። በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ምስጋና በ524 ዓመተ ምህረት መስከረም 14 ቀን የአንድነት ማኅበር በኢየሩሳሌም ሥርዓት ሠርተን አቋቋምን። መመሪያውንም ለመወሰን ተሰበሰብን ሥርዓቱንም ለመወሰን 8ካህናት 8ትዲያቆናት 7ት አበው የወሰኑውን ውሳኔ ያለ ክርክርና ያለመለያየት ተስማምተን ነው። በዚህም ማኅበር ትልቅና ትንሽ ወንዶችና ሴቶች በአንድነት ተባብረን የምንመራበት ሥርዓት ወስነናል ። በዚህም ውሳኔያችን መሠረት ወደ ገዳሙ እንግዳ ቢመጣ 3ት ቀን ያስተናግዱት ከዚህ በኋላ ለመኖር ከፈለገ ያለውን ገንዘብ ለአንድነቱ ገዳም ያስረክብ ካላስረከበ ግን በዓሉን አክብሮ ይሂድ። እንዲህም በአንድነት ቆይቶ ከገዳሙ ለመውጣት የሚፈልግ ከገዳሙ ገንዘብ አይውሰድ በማለት ሰፋ ያለና የተቀደሰ የአንድነት መምሪያና ሕግ ጽፈዋል ። ከዚህ ላይ ታሪኩ አያልቅምና ይህን ከዚህ አቁሜ ከአሁን በፊት የገዳማት አመሠራረት እንዴት ነው በሚለው መጠይቅ በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር18ከገጽ18ላይመነኮሳት በምግባቸውም ሆነ በልብሳቸው ኅብረት እንጂ ልዩነት ፈጽሞ የለም ። በፈቃደኝነት የሚሠሩትና የሚፈጽሙትግን ሦስት ደረጃ አለው። ይሄውም ወጣንያን ማዕከላውያን ፍጹማን ተብለው ይጠሩታል የሚለውን ማስረጃ አሁን ገዳማውያኑ የአንድነት መምሪያ ሲወስኑ አንድ በአንድ ተንትነው ካህናት ዲያቆናት አበው ብለው የገዳማውያኑን መንፈሳዊ ደረጃ አብራርተው ገልጸውታል ።

ስለዚህ ፍጹማን የሚባሉት አበው ናቸው ። ሁኖም የመጀመሪያዋን መሠረት በመጽሔቱ ላይ የተጻፈው ነውና ቀሪውን በመጽሔቱ ተመልከቱ ። አሁን የምንመለከተውም ያንኑ መሠረታዊውን ዓላማ እየተከተሉ አንድነታቸውንና ኅብረታቸውን ጠብቀው በየዘመኑ የመዘገቡትና ያስመዘገቡት ሁሉ ልዩነት የለውም ። ግን የመብታቸውን ሁኔታ በኢየሩሳሌም በየጊዜው እየተቀነሰ የሄደበትን ታሪካዊ ጥብቅ ትእዛዝም መብታቸውን የሚያስጠብቅ በዘመኑ ከነበሩ ነገሥታት በቅደም ተከተል ተጽፏል ።

ሁኖም በቅድሚያ ልንገነዘበው የሚገባን የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ መምሪያ ልዩነትን ለሚፈጥር ሁሉ የሚያወግዝ መሆኑ መታወቅ አለበት ብለን ለማስረዳት ነው አሁን ደግሞ ከተከታዩ ሁለተኛውን ክፍል በመጠኑ አቀርባለሁ ይህም መጽሐፍ ጥንታውያን መጻሕፍት ተብለው ከሚታወቁት መሠረታውያን መጻሕፍት አንዱ ታሪክ ከኔሳት ኡሩሻሌም (የኢየሩሳሌም ቤተ ክርሳቲያን ታሪክ) ከተባለው ትልቅ መጽሐፍ ስለ ኢትዮጵያውያን ቀደምትነት እንዴት አድርጎ በተጣራ ሁኔታ እንደሚያስረዳን እንመልከት ይህም ከገጽ 38 ላይ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሆኑት ዓረቦች በስድስት መቶ 34 (634) ዓመተ ምህረት ታላቅ ኃይል አግኝተው ወደ ኢየሩሳሌም በዘመቱ ጊዜ ሁሉም ድል አድርገው በኡማር እብን አል ኸጣብ መሪነት ኢየሩሳሌምን እጅ በአደረጉ ጊዜ ኡመር እብን አል ኸጣብ በ15ኛው ዓመተ ሕጅሪ የቅዱሳት ቦታዎች ባለመብቶችን ለይቶ ለማወቅና ለመቀበል በደብረ ዘይት ተቀምጦ የተቀበላቸውና ባለመብትነት አውቆ የመዘገባቸው ከላይ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 41 ላይ እንዲህ ይላል ። የኡማር ትእዛዝ ለግሪክ ሊቀ ጳጳሳት ሶፍሮንዩስ ለተባለው መሪ በደብረዘይት ተራራ ላይ ሁኖ የሰጠው አስረጅ ኀልኀታና በቤተ ልሔም በሁሉም ቅዱሳት መካናት (ቦታዎች) ያለ የክርስቲያን ቦታ ከላይ በተጠቀሰው ሊቀ ጳጳሳት ኃላፊነት ሲያጸድቅለት በዚሁ ቦታ የሚገኙ ሌሎችም ዜጎች ባለመብቶች ኩርጅ ሐበሽ ናቸው ። ሲል በሰፊው ጽፎአቸዋል ። ቅዱሳት መካናትን ለመጐብኘት በዓመት የሚመጡ ግን 1ኛ ፈረንጅ ፣ 2ኛ ግብፅ 3ኛ ሶርያ ፣ 4ኛ አርመን ፣ 5ኛ ንስጥሮሳውያን 6ኛ ያዕቆባውያን ፣ 7ኛ ማሮናት ናቸው። እነዚህም ከላይ ለተጠቀሰው ሊቀ ጳጳሳት ተከታዮችናቸው ሲል በሰፊው የጻፈውን ጽሑፍ የኢትዮጵያውያንን ቀዳሚነት በድጋሚ አጉልቶ ያስረዳል ። ይህም በ636 ዓ.ም. የተጻፈ ሲሆን በአርዕስቱ ላይ በተረዳነው መሠረት በቅዱስ ቦታ ኢትዮጵያውያን የአንድነት ማኅበር ከአቋቋሙበት ዘመን በኋላ አንድ መቶ አሥራ ሁለት (ከ112) ዓመት ቆይቶ የተጻፈ መሆኑንም አንባቢዎች ለይተው ሊረዱት ይገባል ። ከዚህ ላይ ታሪኩ እጅግ በጣም ሰፊ ስለሆነ በአጭሩ አንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች የሃይማኖታውያንን ሕግና ሥርዓት ሳይጠብቁ ለግል ጥቅም ሲሉ በሃይማኖት ጥገኝነት በአስመሳይ ቃል አስለቅቀው ራሳቸው ባለመብቶች እንደሆኑ እንረዳለን ። እንዲሁም በዚሁ ታሪክ በቅደም ተከተል በሰፊው በየጊዜው የተጻፈውን አይተን ለመረዳት ቀደም እንደነበሩት የሰውን መብትና ቦታ የሚነጥቁ አሁንም አሉና መጠንቀቅ ይገባናል ።

ይቀጥላል

መምህር ኪዳነ ማርያም ገ/ ሕይወት



## ማሳሰቢያ

«ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ» የሚለው ጽሑፍ ደግሞ እንዲታተም ብዙ አንባቢዎች ስለጠየቁ ከትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 12 ፲፱፻፸ ዓ.ም. እትም የተወሰደ ነው ።

# ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ

በእውነት ጽሑፍ የተጻፈውን እነግርሃለሁ ፤ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም ። ዳን ፤ ፲-፳፩ ።

ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ መላእክት ለሰዎች ብዙ አገልግሎትን ሰጥተዋል ። መንፈሱ ተራቁቶ በፍርሃትም ተውጠ የሚንቀጠቀጠውን ከክፉ ነገር በመጠበቅ ብዙዎችን ረድተዋል ።

ሰው ሊፈጽመው ያሰበውን ተንኮል መላእክት ወደ መልካም ነገር ይለውጡታል ። መላእክት የደስታ የምሥራች ፤ ነጋሪዎች የድኩማን ደጋፊዎች የድሀ አደግ ረዳቶች ናቸው ። በተለይም ቅዱስ ሚካኤል በችግራቸው ጊዜ እየተገኘ የረዳቸውና ከብዙ መቅሰፍትም ያዳናቸው እጅግ ብዙዎች ናቸው በብዙ ቅዱሳት መጻሕፍትም ተጽፏል።

በመጽሐፈ ሔኖክ ስለቅዱስ ሚካኤል በጐ አድራጊነትና ረዳትነት እንዲህ ይላል ። ሰው ባደረገው ነገር ለሕዝቡ ታዛዥ ነውና ከከበሩ መላእክት አንዱ ሚካኤል ነው ። ሄኖክ - ፮፥፭

አዎ ቅዱስ ሚካኤል የተጐዱትን የሚረዳ የተቸገሩትን ሕዝቦች ፈጥኖ የሚያፅናና የተጨነቀችውንም መንፈስ በቅጽበት የሚያድን በመሆኑ ለሰዎች ባደረገው በጐነት ሰማያዊ መልአክ ሲሆን ለሰዎች ግን ቅን ጠባቂ ነውና ታዛዥ ተብሏል ።

ስለዚህ ነው በትንቢተ ዳንኤልም ፤ ከዋነኞቹም አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ተብሎ በችግር ጊዜ ለእርዳታ ምን ያህል ፈጥኖ እንደሚደርስ የተጻፈው ዳን- ፲፥፲፫ ፤

ባጠቃላይ ቅዱስ ሚካኤል ለሰው ልጆች ረዳትና ርኅሩኅ መልአክ በመሆኑ የተጨነቁ ሁሉ ወደእርሱ ልመናቸውን ሲያቀርቡ ከእግዚአብሔር ምሕረትን እየለመነ ከጭንቀታቸው ያሳርፋቸዋል ።



ተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ።

ቅዱስ ሚካኤል በተራዳኢነቱ ከሞቱ ያዳናቸው ከመቅሰፍት የመወራቸው መርገሙን ወደበረከት የለወጠላቸው ብዙዎች ሲሆኑ ፤ በተለይ ፈጥኖ ደራሹ



www.ethiopianorthodox.org

ሚካኤል ሰኔ ፲፪ ቀን ያዳነው ባሕራን የተባለ ወጣት ይገኝበታል ።

ይህም እንዲህ ነው ፤ ከብዙ ዘመናት በፊት በአንድ አገር አንድ ኃብታም ሰው ይኖር ነበር ባጠገቡም የነበረች እንዲት ድሀ ሴት ወንድ ልጅ ወለደ ችና ይህ ሕፃን አመጸኛውን ሀብታም እንደሚወርስ ንግርት ይሰማ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሀብታሙ ሕፃኑን በልዩ ልዩ ዘዴ ከእናቱ ወሰደና በባሕር ጣለው ። ግን እግዚአብሔር ይህን ሕፃን በአንድ የበግ እረኛ አማካይነት አዳነው ።

አሁንም አመጸኛው ሀብታም የሞት ደብዳቤ አስይዞ ወደሀገሩ ላከው ። እግዚአብሔርም ሊያድነው ወዶአልና እንደገና እግዚአብሔር በመልአክተኛው በቅዱስ ሚካኤል አማካይነት የሞቱን ደብዳቤ ወደ ሕይወት ለወጠው ። ከዚህም በላይ «ያ » ሕፃን ልጅ የሀብታሙን ሴት ልጅ እንዲያገባና ሀብቱን እንዲወርስ እግዚአብሔር በመልአክተኛው በሚካኤል አዘጋጀ።ሀብታሙ ከሄደበት ቢመለስ ሁለት ጊዜ እንዲሞት የተመኘለትና እንደሞተም የቆጠረው ሕፃን ሀብቱን ወርሶ፤ልጁን ኦግብቶ ደረሰበዚህ ጊዜ ደንግጦሞተ።የባለጸጋው ሚስት ም በባሏ ሞት ደንግጣ ወዲያው ሞተች ሁለቱም በአንድ ጉድጓድ ገቡ ከዚያ ላይ ነው ቅዱስ ሚካኤል የሰዎች ታዛዥ ሆኖ ምሕረትን ከእግዚአብሔር ይዞ የተገፉትን ሊረዳ ተጋፊዎችን ሊቃወም ይገሠግሳል ተብሎ የተነገረው ።

እግዚአብሔር ሊረዳው የፈለገውን የሰው ሀሳብ ሊያግደው አይችልም እንደተባለው እግዚአብሔር ሊረዳው ያሰበውን ባሕራንን የባለጸጋው ሀሳብ ሊያጠፋው ከቶ አልቻለም ። ጠባቂውና ረዳቱ ተራዳኢው ቅዱስ ሚካኤል ነውና ። «ያ» ባለጸጋ ሀብቱ የተሰጠው የሌላቸውን እንዲረዳበት መሆኑን ባለመገንዘቡ ድሆችን አይረዳበትም ነበር ። እግዚአብሔር ግን ድሆችን ማበልጸግ ፤ ባለጸጎችን ማደህየት የሚችል አምላክ በመሆኑ የድሀዋን ልጅ ሊያበለጽገው በመውደዱ በተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል አማካይነት የባለጸጋውን ሀብት ለድሀዋ ልጅ ለባሕራን አወረሰው ።

ይህ ነገር ቀደም ሲል በግልጽ በመላእክት ልሳን ስለተነገረ ነበረ እግዚአብሔርንና ቅዱስ ሚካኤልን ለመገዳደር ሲል አመጸኛው ሀብታም ባሀራንን ሊያጠፋው የፈለገው ።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሊታደገው የፈለገውን የሰው ሀሳብ ሊጐዳው ስለማይችል ቅዱስ ሚካኤል በተዘዋዋሪ መንገድ የባለጸጋውን ሀብት ከነቤቱ አወረሰው ።

ቅዱስ ሚካኤል በዚህ ጊዜ ነው ለባሀራን ከፍተኛውን እርዳታ ያበረከተለት ። ወደ ባሕር በተጣለ ጊዜ ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቆታል ። የሞቱን ደብዳቤም ወደሕይወት ለውጦታል ።

ወጣቱ የሚመልስበትን መንገድና ሀገር የማያውቀው ስለሆነ ቀናውን መንገድ መርቶታል ።

ስለዚህ ነው መላእክት እንዲህ ዓይነት የግፍ ግፍ በደል ሲደርስ ፈጥነው ስለሚረዱን እኛም በችግራችን ጊዜ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ፈጥናችሁ አድርሱልን በማለት የምናከብራቸው

ቅዱስ ሚካኤል የተማጸኑትን ከብዙ ችግር ያድናቸዋል ። የታመሙትን ይፈውሳቸዋል የተጨነቁትን ያፅናናል ፤ የተሸበሩትን ያረጋጋል ፤ « ያ» ሕፃን እንዲገደል የተፈረደበት በድኅነቱ ነበረ ። ግን እናቱ በታሪክ እንደሚነገርላት ቀደም ብላም በቅዱስ ሚካኤል ረዳትነት የምታምንና ከችግሯም ሁሉ እንዲረዳት ቅዱስ ሚካኤልንየምትጠራ ስለነበረችና ልጅዋምረዳት እንደሌለው ተገንዝባ ቅዱስ ሚካኤል ረዳት እንዲ ዲሆነው አደራ ሰጥታው ስለነበረ አደራ ጠባቂው ቅዱስ ሚካኤል ልጅዋን ከተ ወረወረበት መቅሰፍት ሁሉ በሕይወት ጠብቀላት እጅግ አስፈሪና ኃይለኛ ከነ በረው ባለጸጋ ቁጣ አድኖ የባለጸጋው ንብረት ወራሽ እንዲሆን አደረገላት ያን ጊዜ የነበረው ቅዱስ ሚካኤል ዛሬም ቢሆን የማይለወጥ ስለሆነ አሁንም እርዳታውን አምነው ለሚጠሩት ይደርስላቸዋል ። ልጆቻቸውንም አደራ ከሰጡት በቸርነቱ ከማንኛውም መቅሰፍት ይጠብቃቸዋል ።

የቀደሙት ቅዱስ ሚካኤልን ዕርዳታና አዳኝነት የቀመሱት ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እያሉ የተናገሩትና በቅዱሳት መጻሕፍት የጻፉትም ፈጣኑ ቅዱስ ሚካኤል ፈጥኖ ስለደረሰላቸውና ከችግራቸውም ሁሉ ስለአዳናቸው ነው ።

ዛሬም እኛ ተራዳኢነቱን አምነን እንጥራው ከችግራችንም ሁሉ ሊያድነን የታመነ መልአክ ነው ። ከችግራችንም ሲረዳን ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ሊያድነኝ መጣ ከቅዱስ ሚካኤል በቀር የሚያፅናናኝ የለም እያልን ልንመሰክር እንችላለን ።

የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ። ያድናቸውማል ተብሎ ተጽፎአልና መዝ- ፴፫፡፯

ተስፋ ጥሩነህ



# የሴቶች ዐምድ

## የአፍሪካ ሴቶች ስለ ገጠር ሴቶች እድገት ተወያዩ

በኬንያ ዋና ከተማ በናይሮቢ የገጠር ሴቶች እድገት በሚል ርእስ ከሚያዝያ 19 ቀን እስከ ሚያዝያ 29 ቀን 1971 ትብብር ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ የገጠር ሴቶችን እድገት ለማሳደግ ታስቦ የተሰጠ የመሪነት ትምህርት ሲሆን ይ



ከአምስቱ የዓለም አ.ክ.ግ. ፕሬዝደንቶች አንድዋ ጋናዊት ወ ሮ ጆስቲክ አኒ ጃጂ

ዓ.ም. እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ለ10 ቀናት የተደረገው ትምህርታዊ ስብሰባ አበቃ ።

በዚህም ትምህርታዊ ስብሰባ ከ፣4 የአፍሪካ አህጉር የተወከሉ አባላት ተገኝተዋል ። ይህም ትምህርታዊ ስብሰባ የተዘጋጀው በዓለም አብያተ ክርስቲያናትና በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ህም ትምህርት ምንም እንኳን ጊዜው በጣም አጭር ቢሆንም ብዙ ምሁራን በቦታው ተገኝተው ለተወከሉት ሴቶች ትምህርት አበርክተዋል ።

ከየ ሃገሩ የመጡት ተወካይ ሴቶችም በየ ሃገራቸው ያለው የገጠር ሴቶች መሠረታዊ ችግር ምን እንደሆነ ከገለጡ በኋላ የአብዛኛው የአፍሪካ የገጠር ሴቶች ችግር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል ።

ይህም ችግር ከሞላ ጐደል ሲገለጽ የገጠር ሴቶች በውጭና በቤት ውስጥ ሥራ ሲለፉ ውለው ውሃ ፍለጋ የአንድና የሁለት ሰዓት መንገድ በእግር ተጉዞው ውሃ ማመላለስ፣ በዚያ ላይ ውሃው ንጹህ ስላልሆነ እንደ ፕልሃርዝያና በመሳሰለው በሽታ ቤተሰብ መሰቃየት ። ለማገዶ የሚሆን እንጨት ፍለጋ መንከራተት ፣ ለጠቅላላው ቤተሰብም ሌትና ቀን በሴቶች ጉልበት እየተወቀጠና እየተፈጨ መዘጋጀት ፣ በወንዶች ያለባቸው ተጽእኖ የትምህርት እጦት ፣ በህክምና እጦት በወሊድ ምክንያት የሴቶች ህይወት መቀጨት ፣ ከትምህርት ጉድለት ለቤተሰቦቻቸው የተመጣጠነ ምግብ ያለ ማቅረብና የመሳሰለውም ሆኖ ተገኝቷል ።

በዚሀ ችግር ላይ ተወካዮቹ ብዙ ከተወያዩበት በኋላ ችግሩ የሚፈታበትን ዘዴ በሞያው የበሰሉ ከመንግሥትና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የተወጣጡ ምሁራን ለተወካዮቹ ንግግር አድርገዋል ። ከነዚህም ውስጥ ከ5ቱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማህበር ፕሬዚዳንቶች አንዷ ሚስስ ጆስቲክ አኒጃጂ ፡ ሚስስ ማርታ ብሎንጐና ዶክተር ሚሪያም ዌሪ ከተናገሩት ጥቂቱን እንጠቅሳለን።

ሚስስ ጆስቲክ አኒ ጃጂ ራስን በራስ መርዳት በሚል ርእስ ተነስተው ሲናገሩ ታዳጊው ባህላችን በጊዜው ተቀባይነትን አግኝቶ ይሠራበት የነበረውን ልማድ በማሻሻል እየተጠቀሙበት ነበር ይሁን እንጂ ወጣቱ ትውልድ ደግሞ የነበረውን ዘመናዊ ከሆነ አሠራር ጋር በማዋሐድ አሁን ወዳለንበት ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ሊያደርሰን የቻለው ይኸው ታዳጊው ባህላችን ነው ።

በገጠር የሚኖረው ሕዝብ የሃገሩን ባህልና ቅርስ ተጠብቆ እንዲኖር ሃላፊነት ይኖርበታል ቢሆንም በምርት ረገድ የተመለከትን እንደሆን ከባህል ሲያያዝ እንደመጣው የምርቱ ዘይቤ ጉልበትን ና ጊዜን ከማጥፋቱ በላይ ምርቱም ዝቅተኛና አጥጋቢ አይደለም ፣ እርሻ በዝናብ ብቻ ያተኮረ ከሆነ ሁለት ወይም ሦስ



www.ethiopianorthodox.org

ት ዓመት ድርቅ ቢሆን ከፍተኛ ጉዳት
ሊያስከትል ይችላል ። ስለዚህ በተቻለ
መጠን ራስን በራስ ለመርዳት መጣጣር
ይኖርብናል ።



በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የቤተሰብና
ኅብረተሰብ ፕሮግራም ኃላፊ ወ ት አደሳ ቢላ ጆንስ
ቶን

የዛሬው ስብሰባችንም ዋና ዓላማ የገ
ጠር ሴቶች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲ
ችሉ ለማድረግ ነው ምክንያቱም ሥራ
አልባ ከመሆን ትንሽ ሥራ ይበልጣልና
ድህነት ራሱ ሰውን ተስፋ ማስቆረጥ
ብቻ ሳይሆን ሰው ስለ ራሱ እንዲዋሽና
ዋጋ እንደሌለውም ያደርጋል ። ስለዚህ
ሴቶች ሀገራቸው በምታስገኘው ሃብት
ራሳቸውን በራሳቸው እንዲረዱ ማስተ
ማር ይኖርብናል ። ለምሳሌ የጋናን ሴ
ቶች የወሰድን እንደሆነ ለሊት አሣ እያ
ጠመዱ እስሞኪንግ ፍሽ (አሳት በማያ
ያዝ ከላይ መረብረቢያ አዘጋጅተው በ
መረብረቢያው ላይ አሳውን መጥበስ
ነው) በማዘጋጀት ራሳቸውን በራሳቸው
አሻሽለዋል ። የሌሎችም ሃገር ሴቶች
ራሳቸውን ለማሻሻል መጣር አለባቸው
ራስን በራስ ለማሻሻልም ያልተማረ መ
ማር አለበት ባለው በተፈጥሮ እውቀት
ላይ ትምህ ርት ሲጨመርበት እውቀት
ይሻሻላል ።

ስለዚህም ራስን በራስ ለመርዳት ኋላ
ቀር ሃገሮች በከፍተኛው የቴክኖሎጂ
ውጤት መጠቀም አለባቸው እንጂ የ
ውጭ ሃገር ካፒታል እየተመለከቱ ቊ
ጭ ማለት አያስፈልግም የውጭ ሀገር
ካፒታል ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝ
ናል በይበልጥም አንድን ሃገር ያደኸያ
ል እንጂ አይጠቅምም በማለት ንግግ
ራቸውን ሲቀጥሉ ኋላ ቀር ሃገሮች ችግ
ራቸውን ለመቋቋም ከሚመለከተው እ
ርዳታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል በእርዳታ
ውም ራስን በራስ ለመርዳትና ለመቻል
ሁል ጊዜ ለማኝ ከመሆን ለመዳን ሰዎ
ች በህብረት መሥራት ማምረት አለባ
ቸው ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንደ
ሚባለው ህብረት በጣም አስፈላጊ ነው
ህብረት ካለ ሃገር ታድጋለች ትለማለች
ም ሰዎች ከእድገት ጋር ሲተዋወቁ የመ
ገናኛ መስመሮች ይዘረጋሉ የገጠሩ ወደ
ከተማ የከተማው ወደ ገጠር በመለዋ
ወጥ ገበያ ያድጋል ። የገጠሩም ህብረተ
ሰብ ትምህርት አግኝቶ ራሱን በራሱ እ
ንዲረዳ ያደርገዋል እኛም ማድረግ ያለ
ብን የማናውቀው አዲስ ነገር ከውጭ
እስኪመጣልን ቁጭ ብለን መጠበቅ
ሳይሆን ባለን ሃብት ራሳችንን በራሳች
ን ለመርዳት መጣጣርና መሥራት ነው
በማለት ተናግረዋል ።

ሚስስ ማርታ ቡሎንጐ ደግሞ ንግግ
ራቸውን ሲጀምሩ ስለ ስነ ፍጥረት በመ
ጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን ከሰው



በዓ.አ.ክ.ዓ. የሴቶች ክፍል ዳይሬክተር
የደቡብ አፍሪካ ተወላጅ ወ ት ብርጌድያ ባም

ልጆች ሕይወት ጋር በማዛመድ በሰፊ
ው ከዘረዘሩ በኋላ በከተማም ሆነ በገጠ
ር እድገት በግዴታ አስፈላጊ ነው ። እ
ኛም ሰዎች አንድ ነገር ለማድረግ ከፈ
ለግንም ምንም የሚሳነን ነገር የለም በ
መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደምናነበው
ሰው ጥሩ ነገር እንዲሠራ ሙሉ ስልጣን
ተሰጥቶታል ነገር ግን ጥሩ ሥራ እንጂ
መጥፎ ሥራ እንዲሠራ አይደለም ይሁ
ን እንጂ እኛ ግን ይህንን ያስተዋልን
አንመስልም ። ስለዚሆ ቤተ ክርስቲያን
የእድገት መሪ መሆን ግዴታዋ ነው ።
ከክርስቶስ ተምራለችና በማለት በተለ
ይ ስለ ውሃ ሲገልጹ ውሃ በጣም ጠቃሚ
ነው ይኸውም ለማብሰል ብቻ ሳይሆን
በጠቅላላው ለሕይወት በሙሉ ነው በ



በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የገጠር
አገልግሎት ክፍል ኃላፊ ሚስስ ጃሲ ቴለር

ገጠር እናቶች ውሃና ማገዶ ፍለጋ የብዙ
ሰዓት መንገድ ይጓዛሉ ነገር ግን ከዚህ
ለመገላገል አዲስ ዘዴ እስኪፈለግ ጊዜ
ከሚወስድ ባለን ለመጠቀም ውሃ ውድ
በሆነበት ቦታ ንጹህ የውሃ ማጠራቀሚ
ያ በማዘጋጀት በክረምት ለበጋ የሚያገ
ለግል ውሃ ማጠራቀም ይህ የአጭር
ጊዜ ፕላን ሲሆን የረዥም ጊዜ ፕላን ደ
ግሞ የቧንቧ ውሃ ለማስገባት ፕላን አድ
ርጐ ማስገባት በወሬ ብቻ ያለ ማስቀረ
ት ነው ። ለምሳሌ ያህል ይላሉ ሚስስ
ቡሎንጐ የተባበሩት መንግሥታት ከነ
ሙሉ እቃው ውሃ ለማስገባት እንረዳለ
ን ብለው ከአለቃው ጋር ይነጋገራሉ እ
ርሱም በዚህ በዚያ ይላል ነገር ግን ይህ
በቂ ነው ወይ ? ብለው በመጠየቅ በቂ
አይደለም ችግሩን የሚያውቁትም ሴቶ
ቹ ናቸው ስለዚህ ተቸጋሪዎቹን ሴቶች
ሰብስቦ ምክር ቢጠይቁ ከአለቅየው የ
በለጠ መፍትሔ እንደሚያቀርቡ የታ
ወቀ ነው ። የገጠር ሰዎች ስላልተማሩ
እውቀት የላቸውም ማለት አይቻልም
እንዳውም ከተማረው የበለጠ እውቀት
አላቸው ችግሩን የሚያውቀው ችግሩ
ን የቀመሰ እንጂ ተመልካች አይደለም
በማለት የገጠር ሴቶች ጊዜ በመቆጠብ



ኑሮአቸውን ለማሻሻል የሚችሉበትን
ዘዴ ለተወካዮቹ በሰፊው አስረድተዋ
ል ሚስስ ማርታ ቡሎንጐ በዩኒሴፍ ስለ
እናቶችና በህፃናት ጉዳይ ተወካይ ናቸ
ው ሌላዋ ተናጋሪ ዶክተር ሚሪያም ዌሪ
ስለ አመጋገብ ዘዴ ሲናገሩ የገጠር ሴ
ቶች ለቤተ ሰዎቻቸው ብዙ ምግብ እን
ደሚያቀርቡ እንጂ የአመጋገቡን ዘዴ
እንደሚያውቁ በመጥቀስ የገጠር ሴቶ
ች የምግቡ ዓይነት በሙሉ በእጃቸው
እያለ ከትምህርት ጉድለት የተነሣ የተ
መጣጠነ ምግብ ለቤተ ሰቦቻቸው ሊያ
ቀርቡ አይችሉም ፡ ስለዚህም በገጠር
ብዙ ጉዳት አስከትሏል ። በማለት ሲያ
ብራሩ አንዲት የገጠር ሴት በቤቷ
እንቁላል ካለ እንቁላሉን ሸጣ ለልጅ
ዋ ፋንታ ትገዛለች ባይታሚኑ ያለው
ግን ከፋንታው ሳይሆን ከእንቁላሉ ላይ
ነበር የተመጣጠነ ምግብ ለልጆች በጠ
ቅላላም ለቤተሰብ ያስፈልጋል ። የተመ
ጣጠነ ምግብ ሲባል ከያይነቱ ብዙ ሳይ
ሆን ትንሽ ትንሽ ማለታችን ነው። በማ
ለት ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉ ጥሩ ም
ግብ ለጥሩ ጤና፣ ጥሩ ምግብ ከመድኃኒ
ት ዋጋ የረከሰ ነው በማለት ለተወካዮቹ
የምግብ ዓይነቶችንና የአመጋገብ ህጐ
ችን በጠቅላላ በማብራራት አስረድተ
ዋል ዶክተር ሚሪያም ዌሪ የናይሮቢ
ዩኒቨርስቲ ሌክቸረርና የአንድ ክፍል
ዳይሬክተር ናቸው ።

እንደዚሁም ከዓለም አብያተ ክርስ
ቲያናት ማኅበር ሴቶች በቤተ ክርስቲ
ያንና በህብረተ ሰብ በሚል የሴቶች ክ
ፍል ዴሬክተር የሆኑት ሚስስ ብርጌድ
ያ ባም ። ሴቶች በቤተ ክርስቲያንና በ
ህብረተሰብ ክፍል ሴቶችና የገጠር እድ
ገት የፕሮግራም ጸሐፊ ሚስስ ፕሪስላ
ፓደሊና ከአፍሪካ አብያተ ክርስቲያና
ት የአፍሪካ የገጠር እድገት ፕሮግራም
ኃላፊ ሚስስ ጃሲ ቴለር ከአፍሪካ አብ
ያተ ክርስቲያናት ቤተሰብና ህብረተሰ
ብ ፕሮግራም ሃላፊ የሆኑት ሚስስ አደ
ሳቢላ ጆንስቶን በመሆን ስብሰባው ከተ
ጀመረበት ጊዜእስከ ፍጻሜው እለት ፕ
ሮግራሙን በማቀነባበርና በማስተማር
እንደዚሁም በየቦታው የገጠር ሴቶች
ራሳቸውን በራሳቸው እንዴት እንደሚ
ረዱ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥትና ከ
ሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር የም
ታቋቁመውን ራስን በራስ የመርዳት
ዘዴ ሥራ በማስጐብኘት ሲለፉና ሲደ
ክሙ ከመሰንበታቸውም ሌላ በሴሚና
ሩ የተካፈሉት ሴቶች ወደየ ሃገራቸው
ሂደው ይህንን የገጠር ሴቶች እድገት
ሥራ እንዲያካሂዱ በሚችግራቸው የ
ገንዘብም ሆነ የማቴሪያል ወይም የም
ክር እርዳታ ጥያቄ ላቀረበላቸው ሀገር
ከመርዳት ወደ ኋላ እንደማይሉ ከምክ
ር ጋር አደራቸውን አስተላልፈዋል ።

ከዚህም ሌላ የስብሰባው አላማ በአ
ጭሩ የገጠር ሴቶች የአመራር ዘዴ ለማ
ጠንከርና በአመራር ላይ ያሉትን ሴቶች
እውቀት በማዳበር በሃቀኛ አመራር የገ
ጠር ሴቶች ራሳቸውን በራሳቸው በማ
ስቻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያ
ደርጉና ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለህብ
ረተሰቡ ህልውናና ዋስትና እንደሚሰ
ጡ ታምኖበታል ። በሴሚናሩም ላይ
ቤተ ክርስቲያን በገጠር ስለምትጫወ
ተው የልማት ሚና በሰፊው ተነጋግሮ
በታል ።

ብርሃን ተድላ

## ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፰ የዞረ

ህም ጊዜ ሁሉ ብዙዎች ደቀመዛሙ
ርቶች ይከተሉዋቸው ስለነበረ ጉባኤ
ያቸው ለምን ጊዜም ቢሆን ተቋርጦ የማ
ያውቅ እንደነበረ ይነገራል ።

ሊቁ ከጉባኤ ሊቃውንት ያገኙትን የትም
ህርት ቅርስ በዚህ ዓይነቱ ምርምር ስላደረ
ጁት ከላይ እንደተመለከተው ስሜታቸው
በብልህነት ተቅዋም ላይ መጠናከሩ አስተ
ማማኝ በመሆኑ የንባብ መነሻው ሲታጣ ፣
ምሥጢር ሲሠወር የሚገኘው ከአለቃ ኀሩ
ይ ዘንድ እንደሆነ በጉልህ ይነገር ነበር ፣
ይኸውም የተጠየቁትን ሁሉ ሳያመነቱና
ጊዜ ሳይወስዱ ለማስረዳት ዝግጁ ናቸው
ማለት ነው ።

አለቃ ኀሩይ ፋንታ ሹመቱ የትምህርት
ጉባኤ ብቻ ነው ብለዋል ።

አለቃ ኀሩይ ፋንታ በዕውቀትና በአስተ
ያየት ያደረጉት ምጥቀት በብዙዎች ከመታ
ወቁ የተነሣ የፀዳ እግዚአብሔር አብን ቤተ
ክርስቲያን ልቅና እንዲሾሙ በንጉሥ
ወልደ ጊዮርጊስ ቢጠየቁ መድኃኒታችን
"አባትህ እናትህ ይፈልጉሃል" ላሉት "እ
ባቴም እናቴም የሰማያዊ አባቴን ፈቃድ
የሚፈጽም ነው" እንዳለ ሁሉ ሊቁም ሹመ
ቱ ደቀመዛሙርትና የትምህርት ጉባኤ ና
ቸውና ልቅናውን አልፈልገውም ስላሉ ከ
ሹመትና ከገንዘብ ፍቅር የተላቀቁ ፣ የዚህን
ዓለም ክብር ከንቱነት የተረዱና ያወቁ መ
ሆናቸው ተጠንቶ ተማሪዎቻቸው በልብስ
በምግብ እንዲረዱ ፣ ለእርሳቸውም ከሽል
ማት ጋር የሚያስፈልጋቸው እንዲሰጥ ፣
እንደፈለጉትም ጉባኤያቸውን አስፋፍተው
እንዲያስተምሩ ተደረገ ።

የተረጐሙዋቸው አራቱ ወንጌላት ስለመ
ታተማቸው

አለቃ ኀሩይ ፈንታ በኢየሩሳሌም የሚገ
ኙትን ቅዱሳት መካናት እጅ ከነሡና በደ
ብረ ሊባኖስ ገዳም ለጥቂት ጊዜ ካስተማሩ
በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው መጥተ
ው ከሌሎች ሊቃውንት ጋር አንድም በሚ
ያሰኝ የምሥጢርና የምርምር ሂደት የአራ
ቱን ወንጌላት ንባብ በአማርኛ ተርጉመው
ታትሞ እነሆ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
ካህናትና ምእመናን ይጠቀሙበታል ።

ከዚህም በቀር ከመጻሕፍተ ሊቃውንት
የቄርሎስን መጽሐፍ ንባቡን በሚገባ አድ
ርገው ተርጉመው እንዲታተም ማስረከባ
ቸው ይነገራል ።

በዚህም ቁም ነገርን ባዘለው ተግባራቸ
ው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ
ባለውለታ ናቸው ሊባል ይቻላል ።

ይኸንንና ይኸንን በመሳሰለው አስደሳ
ች ዜና ሕይወታቸውን ሲያስጌጡ ከኖሩ
በኋላም በ1948 ዓ.ም. ሐምሌ 11 ቀን አዲ
ስ አበባ ከተማ ዐርፈው የትርጓሜ መጻሕፍ
ትን ጉባኤ ዘርግተው ባስተማሩበትና መን
ፈሳዊ አገልግሎት ባበረከቱበት በደብረ
ሊባኖስ ገዳም የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት
ተፈጽሟል ።

አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ

## የጤና አምድ

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ጤና ሀብት ነው ፣ ካለን ብዙ ነገሮች
ሁሉ ይበልጣል ፣ አካላችንን ለአእምሮ
አችን ጤናማ አድርገን ለመጠበቅ የም
ናሳልፈው ጊዜ ቢኖር ባከነ አይባልም ።

ጤና ማግኘት የዕድል ወይም የአጋ
ጣሚ ጉዳይ ሳይሆን የአካልና የአእምሮ
እንክብካቤ ውጤት ነው ።

ወ/ት ንብረት አበበ



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቲያኖች ከጋብቻ በፊትና በኋላ ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ

### ሀ ከጋብቻ በፊት

"አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል ማቴ. ም.6.ቁ.33 ።

"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" ዕብ ም. 13 ቁ.4 ማንኛውም ክርስቲያን ፍላጐቱና ምኞቱ አምላኩን እግዚአብሔርን ማመስገንና ማስከበር የመጀመሪያና ፍቁም የእግዚአብሔርን መንግሥት መሆን አለበት ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስለምድራዊ ኑሮው መሳካት መጸለይና ማሰብ ያስፈልጋል ። በተለይም የነገ ተተኪዎች የሚሆኑ ወጣቶች ይህንን ጉዳይ አጥብቀው ማስተዋልና በጸሎታቸውም ሰዓት ማሰብ አለባቸው ። ከጋብቻ በፊት መንፈሳዊ ማኅበራትን የሚያዘወትሩ ፤ በዐውደ ምሕረትም ጥዋትና ማታ የማይታጡ መሆን አለባቸው ዛሬ ግን ምንም ችግር ሳይገጥማቸው በጋብቻ እንኳን ከፍቅሩ የተለዩ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም ምክንያት ሲጠየቁ ሀ በሥራ መብዛት) ለ በቤተሰብ ኃላፊነት ሲያመካኙ ሐ በአንደኛው ተጋቢ ተጽእኖ ማለት ከጋብቻ በኋላአንደኛው ወደ መንፈሳዊ ቦታዎች እንዳይሄድ ተጽእኖ በማድረጉ እንደሆነ ይናገራሉ ።

ጉዳዩ በተለይ የሦስተኛው ነጥብ እጅግ አሳሳቢ ነው መንፈሳዊ ወጣቶች ባሉበት አካባቢ አንዳንድ ሰዎች አልፎ አልፎ ድጋፍ እንዳይሰጡ ካለፉት አንዳንድ ሁኔታዎች ለመገንዘብ እንችላለን ፤ አንገትን እያቅለሰለሱ በስብከት ሰዓት ዐይንን አፍጥጦ በጸሎት ሰዓት አንገትን አጐንብሶ በልብ ግን እግዚአብሔርን እየካዱ በተዘረጋው ወጥመድ ውስጥ የተፈለገው ልጅ (ልጃገረድ) እስኪገባ ድረስ ቀእማኝነት የሌለው የሳምንት ፤ የወር ወይም የዓመት ክርስቲያን ለይቶ ማወቅና ራስን መጠበቅ እግዚአብሔር ካልከለለ በስተቀር በጣም አደገኛ ሁኔታ ነው ። ነገሩ "ጅብ እስኪነክስ ያነክስ" ነውና መጠንቀቁ ያስፈልጋል "እንደ እባብ ልባሞች እንደርግብ የዋህ ሁኑ" ማቴ.ም. 10 ቁ.16

በ1ኛ ቆሮ ም.1 ቁ 12-17 ሐዋርያው ጳውሎስ በኦ.ማኒና በኢ.አማኒ ጋብቻ መስማማቱን እናነባለን ይህንን ያለውም አማኒው (አማኒት) ጽንዐት ኖሯት (ኖሮት) ያላመነውን ክፍል በጌታ እንዲያሳምን እንጂ አማኙ ኢ.አማኒ እንዲሆን አይደለም ታዲያ እንደ ሐዋርያው አባባል ማንም ክርስቲያን በእምነቱ ጠንካራነትና በጸሎቱ ትጋት ከሁሉም በሚበልጠው በእግዚአብሔር ኃይል ታምኖ ቢያደርገው ሙሉ በሙሉ ፍሬ ሊያፈራ ይችላል ፤ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች እንደቀላል ቆጥሮና የራስን የእምነት ጥንካሬ ሳይፈትኑ መግባት ያው ውድቀትንና ከጌታ የተለየ ሕይወትን ያመጣል አንድ ምሳሌ ልጠቅስላችሁ እወዳለሁ ።

እንዲት መንፈሳዊ ልጃገረድን በሀብቱና በጉልማሳነቱ ተማምኖ ሆን ብሎ ለማጥመድ የመጣ አንድ ሰው በእፉ እማኝነቱን አረጋግጦ ብዙ ጊዜ እሷ ወደምትሄድበት መንፈሳዊ ት/ቤት እየሄደ ሲማር ከቆየ በኋላ ልጅቱን ለጋብቻ ጠየቃት እርሷም እንዴት ጥያቄ ልትመልስልኝ ትወዳለህን አለችው እሱም ፈቃደኝነቱን አረጋገጠላት ፤ እሷም ማንን በማን ወደድክ ማለትም ከክርስቶስና ከእኔ በፊት ማንን ወደድክ አለችው እሱም "ከሆድ የተረፈውን በአፍ ይናገሩ"ነውና ክርስቶስን በአንቺ ወደድኩት አላት እሷም እንግዲያውስ እኔን ስትሰለችም ክርስቶስን ትሰለቸዋለህና አዝናለሁ አለችውና ተለያዩ ይባላል። እዚህ ላይ እንድናስተውል የምፈልገው ክርስቲያኖች ከሥጋቸው ክብርና ምቾት ጋር እግዚአብሔርንም በኑሮአቸው ማሰብ አለባቸው ከላይ የተጠቀሰውን አይነት ወጣቶችን እንዴት እናውቃቸዋለን? ብናውቃቸውስ እንዴት እናድርጋቸው? እነዚህ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ የምናውቃቸው ያው በሥራቸው ነው ከፍሬአቸው ታውቁቿቸዋላችሁ ተብሎአልና ። ሲሆንም የእግዚአብሔር ቃል ለማንኛውም ሰው ሊታጠፍ አይገባምና ያለምንም ፍርሃትና ጥርጣሬ ቃለ እግዚአብሔርን ማስተማር ይገባል ። ታዲያ በየዋህነትና በጥበብ ኢ.አማኒያንን አማንያን ለማድረግ እንጂ ተያይዞ ለመካድ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባል "ባላመኑ ስህተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትናወጡ" ተጠንቀቁ 2ኛ ጴጥ.ም.3ቁ.17

### ለ ክርስትያኖች በጋብቻ ጊዜ

መችም ተጋቢዎቹ ክርስቲያኖች ከሆኑ እንኳንስ ጋብቻን ያህል አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ቀርቶ ሰዎች እንኳን አንድ ዝግጅት ሲኖራቸው በዓሉን መርቆ የሚከፍት ክብር ያለው ሰው ጋብዘው ሰውየው በዓሉን መርቆ ይከፍታል ፤ ስለዚህ ተጋቢዎቹም እግዚአብሔር አምላካቸው አዲሱን የሕይወት ምዕራፍ ባርኮና ቀድሶ እንዲከፍት ማድረግ ማለትም ሥርዐተ ተክሊል ወቁርባንን መፈጸም የግድ አለባቸው ተደጋግሞ እንደሚነገረው ሥርዐተ ተክሊል ብቻ ፈጽመው የሚመለሱ ተጋቢዎች አሉ ፤ ይኸ መቸም የተዛባ አፈጻጸም ከመሆኑም በላይ "ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጠመኛነኝ" እንደማለት ይመስላል የምሥጢራተቤ ክማሠሪያቸው ቅዱስ ቁርባን መሆኑ ሲታወቅ ገንጣጥሎ መፈጸሙ ምን ያህል መልካም እንደሚሆን አልገባኝም ከመጋባት በፊት መለያየትንና አመንዝራነትን እያሰቡ ከቅዱስ ቁርባን መራቅ ተገቢ ስላይደለ በዚህ በኩል ሁሉ ሊጠነቀቅ ይገባዋል ።

### ሐ ክርስቲያኖች ከጋብቻ በኋላስ?

በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል ። ቢሆንም ለጊዜው እኔ ለማንሣት የምፈልገው ከብዙዎቹ ነጥቦች ውስጥ ጥቂቶቹን ነው በጸሎት መትጋት ፤ ይኸ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ከኑሮአቸው የመጀመሪያውን ደረጃ ሊይዝ የሚገባው መንፈሳዊውንም ሆነ ሥጋዊውን ፈተና ለመቋቋም የሚረዳ ታላቅ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው ሀ የግል ለ የቤ ክርስቲያንና ቢቻል የቤተሰብ ጸሎት ቢኖራቸው ካልተቻለ ግን ሁለቱን አጥብቀው ቢይዙ መልካም ነው "ሳታቋርጡ ጸልዩ" ተብሏልና 1ኛ ተሰሎ ም.5 ቁ.16 ።

መወያየት ፡- ከጸሎት ቀጥሎ ችግሮችና አለመግባባቶችም ካሉ ውይይት ከጸሎት በኋላ ሊፈታ የሚችል መሣሪያ ነው ። በዚህ ሰዓት ረጋ ያለ መንፈስ ፤ ያለመናናቅ ፤ ትዕግሥት ከሁለቱም ወገን ቢኖር ውይይቱን የበለጠ ፍሬ አዘል ያደርገዋል ልጆችና ቤተሰቦች ካሉ የውይይቱ ተካፋዮች ቢሆኑ መልካም ነው ። ሊረሳ የማይገባ ግን ከውይይቱ በፊትና በኋላ አጠር ያለ ጸሎት መደረግ እንዳለበት ነው ።

መተማመን፡-"አዎን ቢሆን አዎን አይደለም ቢሆን አይደለም" ያዕ ም.5 ቁ.12 ። በኑሮ ሁሉ እንደሌላው ማመን አለበት ፤ ይህ ካልሆነ ግን ጥርጥር በመካከላቸዉ ስለሚኖር ሰላምና ፍቅርን ሊያደፈርስ ይችላል ።

ይቅርታ፡-በስሕተትም ሆነ ተብሎ ለሚፈጸም ስህተት ስህተተኛው የበደለ መሆኑን አውቆ ራሱን መግዛትና በደል የደረሰበትም ይህንኑ ተረድቶ ይቅርታን ማድረግ አለበት ። ይቅርታን ለመጠየቅና ይቅረታን ለማድረግ የተዘጋጀ ልብ ከሁለቱም በኩል መኖር አለበት "በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ"ኤፌ ም.4 ቁ.27

ቀና አስተሳሰብ ፡-ነገሮችን ሁልጊዜ በቀና መጠበቅ ጥሩ ነው ለምሳሌ አንደኛው ወገን ለምሳ ቢዘገይ በሰዓት የተገኘው ወገን በመቆጣት ነገርን ወደሌላ ተርጉሞ ለነገር ተዘጋጅቶ ከመጠበቅ ይልቅ ምክንያቶችን ለማዳመጥ ጊዜ ቢሰጥ የሰይጣንን መንገድያጠፋል "ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን ያዕ.ም.1 ቁ.19 ።

ትምክሕተኝነትን ማስወገድ፡- ተጋቢዎች ይህን ነገር አጥብቀው ማስወገድ አለባቸው ። በዕውቀት ፤ በመልክ ፤ በዘር ፤ በጉሣ ፤ .....ወዘተ መታበይና መመካት ሰላምን ከመንሣቱም ሌላ በጌታ ፊት የተገባ አለመሆኑን በገላትያ ም.6 ቁ 15 እናያለን "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ሌላ ትምክሕት ከኛ ይራቅ" ኑሮየ ይበቃኛል ማለት ፤ ይህ አባባል ክርስቲያ

ናች መሻሻልን አይፈልጉም ባለህበት ሂድ ናቸው ማለት አይደለም ሠርተን ራሳችንንም ሆነ አገራችንን የማሻሻል ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለብን ግን ከአካባቢው በሚታየው አንዳንድ ሁኔታ ከወር ገቢያችን ተመጣጣኝ ያልሆነ ኑሮን ለመኖር መንጠራራት ራስን እንዳለማወቅ ይቆጠራል ። ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ "1ኛ ጴጥ ም.4 ቁ.7 ስለዚህ ቅራኔዎች እንዳይፈጠሩ ሁለቱም ራሳቸውን ቢገዙና በመጠን እንዲኖሩ ኃላፊነት አለባቸው ።

አንዱ ስለሌላው ይጸልይ ፡-በአንዳንድ ሁኔታዎችና ስሕተቶች የአንድ መንፈሳዊ ሕይወት ሲቀዘቅዝና ከተለመደው ሁኔታና ጠባይ የተለየ በሚሆን ጊዜ ተቃራኒው ያታ ነገሩን በጸሎት ወደ ጌታ ማመልከት አለበት ይኸ ደግሞ ካልተሳካ ለቤተሰቡ መምሕረ ንስሓ ነግሮ እንዲመክር ማድረግ እንጂ መተቻቸትና መነታቀፍ ነገሩን ከማባባስ ሌላ በበለጠ ከጌታ እንዲርቅ (እንድትርቅ) ማድረግ ሊሆን ይችላል ።

ወ ት የልፍ ዓለም ተስፋዩ



# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

## የከፋ ሀገረ ስብከት አብያተ ክርስቲያናት

ጂማ፡- በከፋ ሀ/ስብከት ሦስት መቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገኙ ተገለጠ ። የከፋ አውራጃዎች 6 ሲሆኑ በእያንዳንዱ አውራጃ ስንት አ/ክርስቲያናት እንዳሉ እንደሚከተለው እናሳያለን፡-

በጂማ አውራጃ 25
በሊሙ አውራጃ 85
በከፋ አውራጃ 73
በኩሎ አውራጃ 27
በማጂ አውራጃ 8
በጊሚራ አውራጃ 12

በርእሰ ከተማው በጂማ ደግሞ 6 አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ግን ድምራው በላይ ከተጠቀሱት ጋር ይሆናል ሲሉ አዲሱ የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ገልጠዋል በዚህ አጋጣሚ ሌሎችም አባቶች የሚመሩአቸውን አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ዓይነት በትክክል ቢቆጥሩ ሐዋርያዊ ሥራቸውን



የከፋ ሀ ስብከት ጳጳስ አቡነ ኤልሳዕ

ለማፋጠንና የምእመናንን ብዛት ለማወቅ የሚረዳቸው መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን ይህ ብቻ አይደለም የካህናትንም ትክክለኛ ቁጥር ቢመዘግቡ መልካም ነው እንላለን ።

## የኅብረተ ሰብአውያት ሀገሮች አብያተ ክርስቲያናት ምስክርነታቸውን ሰጡ

ፕራግ ፡- የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባላት የሆኑ የሶሻሊስት ሀገሮች አብያተ ክርስቲያናት ከመጋቢት 19 21 ቀን 1971 ዓ.ም. በቾኮዝላቫኪያ ዋና ከተማ በፕራግ ስብሰባ አድርገው በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች ስለ ክርስትና እምነታቸው እንዴት መመስከር እንደሚችሉ ተወያይተዋል ። ስብሰባውን የተካፈሉ ተወካዮች አርባ አራት አባሎች ነበሩ ፤ ከእነርሱም መካከል የነገረ መለኮት ሊቃውንት ፤ ቀሳውስትና የቤተ ክርስቲያን አለቆች ተገኝተዋል ። የሌኒንግራድና የኖብጎሮድ መትሮፖሊታን አንቶኒ በጉባኤውላይእንደሚከተለውተናግረዋል "በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ሃይማኖቶች ዕንቅፋቶች አይደሉም ግን ስለ ሰላምና ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ለሚደረገው ትግል መነሻና መድረሻ ናቸው በግልም ሆነ በኅብረት በመንፈሳዊ ሥርዐት የታነፀው የክርስቲያኖች ምሳሌነትና ምስክርነት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ኦርቶዶክሳዊው መሪ አስረድተዋል ። ጉባኤው በሚቀጥለው ዓመት በተመሳሳይ ርእስ ለመወያየት በአውስትራልያ ይሰበሰባል "መንግሥትህ ትምጣ' ሲል ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ስር ቪስ ቁ10 46ኛ ዓመት ገለጠ ።

## ክርስቲያኖች ስለጦር መሣሪያ ቅነሳ ስምምነት አወጡ

ጄኔቫ፡- ከሦስት ቀን ጉባኤ ፍጻሜ በኋላ የሩሲያና የአሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስለ ጦር መሣሪያ ቅነሳ አንድ አይነት ስምምነት ያደረጉ መሆናቸው ተነገረ ። ጉባኤው የተካሄደው ከመጋቢት 27-29 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ) በጄኔባ ነበር ። የሁለቱ ሀገሮች ክርስቲያናውያን መሪዎች "አሁንም ቢሆን እጅግ የሚያሰጉና የሚያስፈሩ የጦር መሣሪያዎች እየተጨመሩ በመሄድ ላይ ናቸው የሰውንም ዘር ወደ አስጊ ሁኔታ አድርሰውታል ። ይህን ድርጊት፡- በአንድ ድምፅ በእግዚአብሔር ስም እንቃወማለን" ብለዋል ኢኪዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቢስ ቁ.10 ሚያዝያ 5 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ)

## የሩሲያ ቤተ ክህነት 50.000 መጽሐፍ ቅዱስ አሳተመ

ሞስኮ፡- የሞስኮ ቤተ ክህነት የሕትመት ድርጅት ክፍል ባለፈው የካቲት ወር ሃምሳ ሺህ ሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮፒ ያሳተመና ለሩሲያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ያደለ መሆኑንየፓትሪያርክ ሊቀ ጳጳስ ፒቲሪም አስታወቁ ። ይህ አሁን የወጣው መጽሐፍ ቅዱስ ከጦርነቱ ወዲህ ሲታተም አራተኛ ጊዜው ነው ።


ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ
ቁ.9 መጋቢት 29 1979 (እ.ኤ)



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፤ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፤ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ



የኑሮ ጓደኛ ፈላጊው አቶ አሰፋ ብዙ ወርቅ

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ጸጋና በረከት ያድላችሁ ዘንድ ምኞቴ ነው ፤ ባለፈው እትማችሁ ላይ ምን እንርዳዎ የሚል ጽሑፍ አንብቤ በጣም ጠቃሚና አስደሳች መልእክት ያዘለች መሆኗን በዚህ አጋጣሚ ልገልጽ እወዳለሁ ፤ ይኸውም አርእስት ብዙ የሐሳብና የጭንቀት ማኅበር ሆነው ሃሳባቸውንና ችግራቸውን ለመግለጽ አማካሪ ላጡ ሃሳብ መግለጫ ትሆናለች ብዬ ስለማምን ነው ።

ስለዚህ እኔም አንዱ በሀሳብና በጭንቀት የምገኝ ያለብኝን ችግር በምን እንርዳዎ ዐምድ አማካኝነት መፍትሔ እንደማገኝ በመተማመን እግዚአብሔር አምላካችን ሲፈጥረን ብዙ ተባዙ ባለው መለኮታዊ ቃል እኔም ይኸንኑ ምርኩዝ በማድረግ አንዲት የኑሮ ጓደኛ የምትሆነኝን ወጣት አግኝቼ የተቀደሰና ሰላም የሰፈነበት ኑሮ ለመኖር ፈቃደኛ ነበርኩ ታዲያ ምን ያደርጋል እኔ በተፈጥሮዬ ሴቶችን መቅረብና ማነጋገር ስለምፈራ የብቸኝነት ኑሮዬን ተጋትሬዋለሁ ስለዚህ እንደ እኔ በብቸኝነት የምትኖር እግዚአብሔርን የምታከብርና የምታመሰግን ቤተ ክርስቲያን ወዳድ የታመመ ጠያቂ ይነስም ይብዛ ደመወዝ ያላት ተመክራ የምትመክር ሚስት እፈልጋለሁ ፎቶግራፌንም የላኩት በዕውነት ፈላጊ መሆኔን ለማረጋገጥ ነው ፤ ፈላጊዎች አድራሻዬን ቢፈልጉ
አሰፋ ብዙወርቅ የፖ.ሣ.ቁ.802
የስ.ቁ.122176 12-20-11

ምሳሌ ሰሎሞን 19፡14" ቤትና ባለጠጋነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሣሉ (ይገኛሉ) አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት ይላል ስለዚህም እንዲህ ያለችውን የኑሮ ጓደኛ ለማግኘት ከምርጫው ጋር ጸሎትም ያስፈልጋል ።

ደግሞም ጠያቂው በሚሉት መሠረት ሁሉን ነገር አሟልታ የያዘች የኑሮ ጓደኛ (ሚስት) ለማግኘት የሚያስችል የራስዎም ማንነትና የአቋም ማለትም የመልካም ጠባይና የሙያ (ወዘተ) መስተካከል ጉዳይ ጭምር መሆኑን አይዘንጉ ። በምርጫዎም ሆነ በጸሎትዎ ስምረት መልካም የኑሮ ጓደኛ ለማግኘት እንዲበቁ እንመኝልዎታለን ።

ከአቶ አሰፋ ብዙ ወርቅ ጋር የኑሮ ጓደኝነትን ለመመሥረት የምትፈልግ እኅት ብትኖር አንደኛ በቀጥታ ለእርሳቸው በአድራሻቸው መጻፍ ወይም ስልክ መደወል ትችላለች ። ከዚህም ሌላ ለ"ምን እንርዳዎ" ዐምድ አዘጋጅ ብትጽፍ ሥዕሏንም (ፎቶግራፍዋን) ብትልክ በመጽሔታችን ለማውጣት ዝግጁዎች ነን ።



# የተፈጥሮ መረዳዳት

በተፈጥሮ ሕግ የእርስ በርስ መረዳዳት ስላለ የሰውን ሕይወት ብንመረምር ያለ ሰው ርዳታ ካለበት ደረጃ የደረሰ አናገኝም ስለዚህ በሰው ተረድተን አናውቅምን? የማያቋርጠው የወላጆቻችን እንክብካቤ ጠባዮችንን አላነጸውምን? መምህራችን ድል አድራጊ እንድንሆን አልረዳንምን? አሠሪያችንስ የተለየ ችሎታ እንድናሳይ ዕድል በመስጠት አልረዳንምን? ለእኛም ለቤተሰባችንም የሚገባንን ክብር በመስጠት አንድነት እንዲኖረን ጐረቤቶቻችን አልጣሩምን? ሌላው ቀርቶ ያላሰብነው እንግዳ የሚያስፈልገንን ርዳታ ሰጥቶን ይሆናል ። እነዚህ ሰዎች በሕይወታችን ለውጥ እንዳስከተሉልን ብናስብ እኛም ለሌሎች ለሚያጋጥሙን ሰዎች ተመሳሳይ ርዳታ እንዳደረግን ወይንም ልናደርግ እንደምንችል መገንዘብ አለብን ።

ይህንን ያልተገነዘብን ሁሉ መልካም አድራጐት በአደጋና የተለየ ጥረት በሚያስፈልግበት ጊዜ ብቻ መፈጸም እንዳለበት አድርገን እናስብ ይሆናል ። ሌሎችን ለመርዳት በአጋጣሚና በአደጋ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ችግር ሊሆን ይገባል ። ሌሎች ብዙዎች አጋጣሚዎች አሉ ስለዚህ ሌሎችን በመርዳት በማፅናናት ፤ በመምራት ያደረግነው ጥረት ምን ያህል ለውጥ እንዳስገኘ በማስታወስ ጥረታችን ምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ እንችላለን የርዳታ ትንሽ የለውም ሁለት ሳንቲም የሰጠችው መበለት ያላትን ስለሰጠች ብዙ ከሰጡት ይልቅ እርሷ ተመስገነች ስለዚህ ለልጆቻችን የምናደርገው መልካም ጥረት ልጆቻችን ጥሩ ጠባይ እንዲኖራቸው ይረዳል ከልጆቻችን ጋር በመዝናናት የምናደርገው የእግር ጉዞ ከእነርሱ ጋር አብሮ መሆን እነርሱን ምን ያህል ማፍቀራችንና የሚሉትን ማዳመጣችን የወደፊት ኑሮአቸው በመልካም ጠባይ የታነጸ እንዲሆን ያደርገዋል ።

የወላጅ ታማኝነት ስግብግብ ወይም ሁሉ ለኔ ባይ አለመሆኑና ተለዋዋጭ ያልሆነ ጠባይ ለልጆች ጥሩ ምሳሌነት አለው ። ይህ ከሆነ የራስን ወላጆች በማክበር አባትና እናትህን አክብር የሚለውን ትእዛዝ ልጆች እንዲያከብሩት ማድረግ ይቻላል ።

ከዚህም በላይ ባልና ሚስት የሚያደርጉት መመካከር ፤ የሐሳብ መለዋወጥ ፤ ያላቸው የእርስ በርስ ፍቅር ለኑሮአቸው አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ።

በቤተሰብ መካከል የእያንዳንዱ አባል ተረቃቅሮ መኖርንና የእርስ በርስ መተሳሰብን የሚተካ ከመልካም ጠባይ በቀር ሌላ ምንም ነገር የለውም ።

በሌላ በኩል ደግሞ ልንኖርበት የምንፈልገው ሠፈር ከተፈጥሮና ከሰው ጉልበት ሀብቶች የበለጠ የሚያስፈልገው ነገር አለ ። ይኸውም እርስ በርስ በመረዳዳት የችግረኞች ኑሮ የሚሻሻልበትን መንገድ መፈለግ ነው በሠፈራችን እያንዳንዳችን ለሌላው ጐረቤት ስለሆንን በየዕለቱ በምንፈጽመው አድራጐት ለእኛ ሊኖረን የምንሻውን ሁሉ ለጐረቤታችንም እንዲኖረው መሻት ይገባናል ። መልካም ጠባይም ማሳየት ይፈለግብናል ።

ይህ ብቻ አይደለም ከሰፈራችን ውጭ ከመቸውም ይልቅ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ጉዞ እናደርጋለን የተለያዩ ሰዎችም ያጋጥሙናል የምናገኛቸውም ሰዎች መሠረታዊ ፍላጐታቸው በቅርብ ካሉት ጐረቤቶቻችን ፍላጎት ጋር ልዩነት የለውም በዚህ መንገድ ሁሉንም በአንድ ዐይን ልናያቸው መልካም ጠባይም ልናሳያቸው ይገባል ። አቅማችንም በፈቀደ መጠን የችግራቸውና የደስታቸው ተካፋዮች መሆን የዘወትር አላማችን መሆን አለበት ። ከዚህም የተነሳ በያንዳንዳችን መሀከል ያለውን ልዩነት በመቀበልና በማክበር ተመልክተን ከልዩነት የምናገኘውን ትምህርት በመቅሰም ሕይወታችንን በበለጠ ልናበለፅገው ይገባናል ።

ሰው ሲባል በጠቅላላ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው ስለዚህ የሰዎች ወንድማማችነትና እህትማማችነት በየትም ሥፍራ ያለ ይሁንእንጂ በዚህች በተለዋዋጭ ዓለም አንዳንድ የማይለወጡ ልማዶች አሉ ። ለምሳሌ ያህል ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረና ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች የተወለደ ሲሆን እገሌ የእናትና የአባቴ ልጅ ስለሆነ ወንድሜ ነው እገሊትም የአባቴና የእናቴ ልጅ ስለሆነች እህቴ ናት እገሌም የአባቴ የወንድም ልጅ ስለሆነ የአጐቴ ልጅ ነው ፤ እገሊትም የእናቴ እህት ልጅ ስለሆነች የአክስቴ ልጅ ነች ፤ እነ እገሌም የቅርብ ዘመዶቼ ናቸው የማለትና የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ ወንድሙና እህቱ መሆኑን በመዘንጋት በመካከሉ ልዩነትን መፍጠሩ ነው ይህንን ግን ሰው በልማድ የፈጠረው እንጂ ከተፈጥሮ ሕግ ያላገኘው በመሆኑ ሊሠረዝ የሚገባው አጉል ልማድ ነው ። ስለዚህ ይህንን እኛ ልንፈጽመው የሚገባን አይደለም የሚለውን የተሳሳተ አስተያየት ልንሰጥ አይገባንም ።

የሚቀርቡት ሀሳቦች ሁሉ በልማድ ሳይሆን ቀጥተኛ መንገድን ተከትለው ቢሄዱ መልካም ነበር ነገር ግን ዓለም ከቀን ወደ ቀን እየተለዋወጠች በመሄዷ እኛንም ከአንድ ሥር ጥላን ስለምትገዝ ህሕወታችንም ሥራችንም ተዘበራርቋል ።

ስለዚህ ምን ማድረግ ይገባናል? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን በመጀመሪያ በጎነህያለውን እንደሚፈልገው መርዳት ነው ። ይህንን ብንሠራ በርከት ያሉ ጎረቤቶች ይኖሩናል ። ምናልባት ለአንድ ሰው አንድ ቀን ርዳታ እናደርግ ይሆናል ነገር ግን ሁሉንም ለመርዳት እንችልም ማለት የለብንም እነሱም ያጋጠማቸውን ችግር ሁሉ እንድናቃልላቸው ይፈልጉ ይሆናል በተቻለን መጠን ይህንን የማናደርግ ከሆነ እያንዳንዱ ሕብረተሰብ ተፈላጊ አለመሆኑን መዘንጋታችን ነው ።

ስለዚህ ሰዎች ተቸግረው ሲያለቅሱ ስናይዝም ብለን ማለፍ የለብንም የአይናቸውን ዕንባ አብሰን ሕይወታቸው በሥራ እንዲለወጥ ማድረግ አለብን ።

ሚኮር የተባለው ሊቅ "ክርስትና ወደፊት አገኘዋለሁ ተብሎ የሚጠበቅ ሳይሆን ራሱ የሚኖርበት ዓለም ነው" ብሎ ተናግሯል እንዳለውም ስርቆ ሳያስሩ ፤ ሌላውን ሳያገለግሉ ፤ ሌላውንም ሳይረዱ በክርስትና ዓለም ውስጥ እኖራለሁ ማለት ክርስትናን ወደፊት አገኛለሁ ብሎ እንደመጠበቅ ይቆጠራል ።

የዘመኑ ሳይንስም ቢሆን እርስ በርስ መረዳዳትና አንዱ ሌላውን ማገልገል እንደሚገባ ይጠቁማል ።

ጁሊያን ሑክስሊ የተባለው ምሁር "የሃይማኖትና የሳይንስ ስብከት በአንድ ላይ የሚሰበክበት ጊዜ እሩቅ አይደለም ሁለቱም የተለያየ አቋም የላቸውም ሁሉም የሰው ልጆች መመሪያዎች ናቸው በሃይማኖት ትምህርት የተራቀቀው ለዓለም ጀርባውን ሰጥቶ አያልፍም እንዲሁም በጥበብ ብቻ የሚያምነው በመንፈሳዊና በሃይማኖት የተመሠረተች ዓለም መሆኗን አይክድም" ብሏል ።

እንዳለውም ሁለቱም ሕብረተሰብን የሚጠቅም ሥራ ካልሠሩ ከዓለም እያመለጡም ቢፈልጉም ባይፈልጉም ከዓለም ውስጥ ናቸውና ።ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ለውጥን አይፈልጉም ስለዚህም ከዓለም ራሳቸውን ለመደበቅ ያስባሉ። ነገሩ ሁሉ እንደ ወህኒ ቤት መስሎ ይታያቸዋል የተለመደውንና ምቹውን ሥራ መረከብ እንጂ አዲስ የሆነው ሁሉ አያስደስታቸውም ።

ሌሎቹ ከዓለም ለውጥ ራሳቸውን ገለል በማድረግ በነገሩ ያለመግባባት ይገኛሉ ። ጥቂቶቹም የአልኮልና የልዩ ልዩ ኪኒኖች ተገዢ ሆነዋል ። ጥቂቶቹም ራሳቸውን ከህብረተሰቡ በመለየት ገለልተኛ አድርገውታል ። እንዲሁም ከኅብረተሰቡ ውጪ የሆነ ልዩ ሕብረተሰብ ለማበጀት ያስባሉ ።

ይህ የማይፈለግ አርጌ አስተሳሰብ ስለሆነማንኛውም ሰው ችሎታ ያለው በችሎታው ፤ ጉልበት ያለው በጉልበቱ ፤ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ ፤ ዕውቀት ያለው በዕውቀቱ አገሩንና ወገኑን እንዲረዳ ቤተ ክርስቲያን መልእክቷን ታስተላልፋለች ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ይህን ያውቁ ኖሯል ?

(እጅጉ ረታ)

ታሪኩን ከመጀመሪያው የተከታተላችሁ አንባቢዎች እንደምታስታውሱት "ሚራክልስ ኦፍ ጐድ" ከተባለው መጽሐፍ ተርጉሜ በቁጥር "15"ና "17" ትንሣኤ መጽሔት ያቀረብኳቸው አስደናቂ ታሪኮች መደበኛ አርገው የሚያወሱት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን መግለጥ ብቻ ነበር ። ባለፈው እትም ግን የመላእክትና የጌታ መግለጥ እንዲሁም አንዳንድ አስደናቂ ነገሮች ተጨምረውበት መቅረቡ ይታወሳል ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሠፈርኳቸውም ታሪኮች በዚያው ዓይነት የቀረቡ መሆናቸውን ለአንባቢዎች ልገልጥ እወዳለሁ ።

ታሪኩም እንደሚከተለው ነው ።

1 በ30/8/367 ዓ.ም. እግዚአብሔር አብ ከደመና በላይ ሆኖ ሊታወቀው የቤተ ክርስቲያን አባት ለቅዱስ ቆጵርያኖስ ታይቷል ።

2 በ398 ዓ.ም. ገደማ በቀጰዶቅያ ውስጥ ጐረም በተባለ ቦታ አንድ



www.ethiopianorthodox.org

የታዘዘ የእግዚአብሔር መልአክ ለቅዱስ አኖፍሪዮስ የክርስቶስን ሥጋና ደም በየጊዜው ያቀብለው ነበር ይባላል ።

3/ ከሮሜ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ ትልቁ ጎርጎርዮስ በ589 ዓ.ም. ዓለም በቃኝ ብሎ ከዋሻ ዘግቶ ነበር ። ታዲያ በዚያ የነበሩ ምዕመናን የት እንዳለ ጨንቋቸው ሲፈልጉት በዘጋበት ዋሻ አናት ላይ የብርሃን ደመና ዓምድ ተተክሎ በዚያ ላይ መላእክት ሲወርዱ ሲወጡ ሊያዩ ችለዋል ።

4/ በ627 ዓ.ም. የቢዛንት (ቁስጥንጥንያ) ንጉሠ ነገሥት የነበረው ኤራቅሊጎስ (ሕርቃል) በድል አድራጊነት ሀገር ቅድስት እንደደረሰ ፤ የከተማዪቱን (ኢየሩሳሌምን) በር መልአኩ ሲከፍትለት ለማየት ችሏል ።

5 በ648 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ለቅዱስ ዩዴቁስና ለቅዱስ ዩስሩር - ሜር ጌታ ምንም - ምን የሌለው ምስኪን ድኃ መስሎ ሦስት ጊዜ ተገልጦላቸዋል ።

6 በ651 ዓ.ም. የእንገሎ-ሳክሶንና የኬልት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፤ እየተባለ የሚጠራው ኩትበርት ከዕለታት ባንዱ ሌሊት መላእክት አንዲት ነፍስ ይዘው ወደ ሰማይ ሲወጡ (ሲያርጉ) ለማየት በቅቷል።

7 በ675 ዓ.ም. ላይ ጌታ በሕፃን መልክ ሆኖ በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ለቅዱስ አል ተገልጦ ታይቷል ።

8 በ814 ዓ.ም. የሰሜን ክፍል (እስካንዲኔቪያ) ታላቁ ሐዋርያ እየተባለ ለሚጠራው ለቅዱስ እንስካር በበዓለ ጰራቅሊጦስ (በዓለ ሃምሳ) ዕለት በዋዜማው ሌሊቱን መድኃኒታችን ተገልጦ ታይቷል ።

9/ በ973 ዓ.ም. በጀርመን ሀገር ኦግሰበርግ ውስጥ ቅዱስ ኡልሪክ የተባለው ሰው በጠና ታሞ ሳለ እነሆ ሁለት መላእክት ጻሕልና ጽዋ ይዘው ይታዩታል ፤ ወዲያውም በሚያንፀባርቅ የብርሃን ፀዳል የተከበበ እጅ (የጌታ) ሲባርክ ታይቶታል ።

10/ በ1008 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሐገር ባለንቺንስ በተባለው መንደር የቸነፈር በሽታ ገብቶ ነበር ።በዚያም ወቅት አንድ ቀን ምዕመናን ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ እመቤታችን ተገልጣ ታይታቸዋለች ።

11/ በ1060 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሐገር ኤስፔን በተባለች መንደር ጌታና እመቤታችን ተገልጠው ታይተዋል ።

12/ ከ16.1 -17. 4. 1095 በፈረንሳይ ሀገር ውስጥ አራስ በተባለች መንደር ነዋሪዎች በሙሉ እመቤታችን በደመና ላይ ደጋግማ እየተገለጠች ብዙ ጊዜ ትታያቸው ነበር ይባላል።

13/ በ1100 ዓ.ም. ገደማ እመቤታችን ቅ.ድንግል ማርያም በእንግሊዝ ሀገር ካንተርበሪ ውስጥ ለቅዱስ አንሰልም ደጋግማ ትገለጥለት ነበር ይባላል ።

14/ በ1110 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር ክሌሩ በተባለ ቦታ እመቤታችን ቅ.ድንግል ማርያም ሕፃን ልጅዋን እንደታቀፈች ሆናና መላእክት አጅበዋት ለቅ.ቤርናርድ ተገልጣ ታይታለች ።

15 በ1117 ዓ.ም. በኢጣልያ ሀገር ክሪምና ውስጥ አንድ ፤ የአንድ ዓመት ሕፃን በድንገት አፉን ከፍቶ አንዲት እንደፀሐይ የምታበራ ሴት (እመቤታችን) ያየ መሆኑን ገልጦ ሁኔታውን በዝርዝር አስረዳ ።



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org